# የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ ትንተና በሽካቾ ብሔረሰብ[1]

# Analysis of the Gudo Kesoo Folk Belief Performance in the Sheko Ethnic Group

ግሩም አረዳ[2]፣ ዓለሙ ካሣዬ[3] እና የኔዓለም አረዶ[4]
**Girum Areda, Alemu Kassaye, and Yenealem Aredo**

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዓላማ የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ሥርዓተ ክዋኔን መተንተን ነው፡፡ ዓላማውን ለማሳካት፤ የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ሥርዓተ ክዋኔ ሂደት ምን ይመስላል? ለምንስ ይከወናል? በጉዶ ኬሶ ክዋኔ ላይ የሚቀርቡ ቴክስቶች፣ ቁሶችና ድርጊቶች ምን አይነት ትዕምርት አላቸው? ጉዶ ኬሶ በመከወኑ የሚገኘው ጥቅምና ባይከወን ሊደርስ የሚችለው ጉዳት እንዴት ይገለጻል? የሚሉ የምርምር ጥያቄዎች ተነስተው በጥናቱ መልስ አግኝተዋል፡፡ ጥናቱ በባህሪው ዓይነታዊ (Qualitative) ምርምር ሲሆን ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ[5]ና የቡድን ውይይት[6]ን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሟል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያላቸውን ትርጉም ለመፈከር የክዋኔ መርና የትዕምርት ንድፈ ሀሳቦች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ጥናቱ የሀገረሰባዊ እምነቱን ክዋኔ፣ የክዋኔውን ተከታታይና ተለጣጣቂ ሁነቶችን ለመተንተን ገላጭ (Descriptive) የመረጃ መተንተኛ ዘዴን ተከትሏል፡፡ የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ለፈጣሪ (Yerochi) ከፍ ባለ ተራራ ላይ የሚቀርብ የመስዋዕት ሥርዓተ ክዋኔ ነው፡፡ የሸካቾ ብሔረሰብ በጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ አማካኝነት፤ የአካባቢው ሰላም እንይናጋ ፣ ጤና ደህንነቱ እንዳይቃወስ፣ ከፈጣሪው ጋር ያለው መልካም ግንኙነት እንዳይበላሽ፣ ማህበራዊና ባህላዊ አኗኗሩ እንዳይሳከር፣ ሰማይ ምድሩ እንዲታረቅ፣ እህል ገንዘቡ ረድኤት እንዲወርድበት፣ እንስሳቱ እንዲረቡ፣ ወተት እሸቱ እንዲበረክት የሚለማመንበትና ስነ ምህዳሩን የሚያስጠብቅበት ስርዓተ ክዋኔ እንደሆነ ጥናቱ አመላክቷል፡፡

**ቁልፍ ቃላት፤** ጉዶ ኬሶ ፣ ሀገረሰባዊ እምነት፣ መንጻት፣ መስዋዕት፣ ሥርዓተ ክዋኔ ፣ ትዕምርት

---

[1] ይህ ርዕስ "የጉዶ ኬሶ እና የሸንበተ ቆጮ ሀገረሰባዊ እምነቶች ክዋኔ በሸካቾ ብሔረሰብ" በሚል ለሶስተኛ ዲግሪ እየተደረገ ካለው የማሟያ ጥናት፣ አንደኛውን ንዑስ ዓላማ በመውሰድ ለዚህ መጣጥፍ በሚመጥን መልኩ የቀረበ ነው፡፡

[2] በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ በፎክሎር ስድስተኛ ዓመት የፒ.ኤች.ዲ ተማሪ፣ girumee@gmail.com

[3] በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፎክሎር መምህር፤አዲስ አበባ፣ alemukas@gmail.com

[4] በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፎክሎር መምህር፤አዲስ አበባ፣ yenealem2006@yaho.com

[5] በዚህ ጥናት ቃለ መጠይቅ የሚለው (ቃ.መ) በሚል አጥሯል፡፡

[6] በዚህ ጥናት የቡድን ውይይት የሚለው (ቡ.ው) በሚል አጥሯል፡፡

**Abstract**

The purpose of this study was to analyze the performance of Gudo Kesoo Folk Belief in the Sheko ethnic group. To achieve this purpose, the following research questions were posited and answered in the process of this study. What is the process in performing Gudo Kesoo folk belief? Why do the people perform it? What kind of symbols do the texts, materials, and actions presented on Gudo Kesoo's performance have? What are the benefits of performing Gudo Kesoo, and what are the adverse influences of not performing Gudo Kesoo? These research questions were raised and answered in the study. The study employed a qualitative research approach. To collect data, three data-gathering tools, namely observation, interview, and focus group discussion, were utilized. Performance and symbolism theories were used to interpret the data collected from the field. The study followed a descriptive data analysis method to analyze the performance of the folk belief and the processes of the events in the performance. The folk belief of Gudo Kesoo is a ritual ceremony offered to the Creator (Yerochi) on a high mountain. It has been found out that the Shekacho nation celebrates the Gudo Keso ritual ceremony with the belief that it keeps the local peace, health, and safety, and it has a good relationship with the Creator. They also perform the ritual so that the social and cultural lifestyle will not be ruined, the grain and the money will be blessed, the sky and the earth will be reconciled, the animals will grow, the milk and new products will become abundant, and the ecosystem will be protected.

**Keywords:** Gudo Kesoo, Folk Belief, Purification, Sacrifice, Performance, Symbolism

## 1. የጥናቱ ዳራ

እምነት የሚለው ቃል ተደራራቢ ጽንሰ ሀሳቦችን የያዘና ሰፊ ማህበራዊ መሰረት ያለው በመሆኑ በአንድ ቃል መግለጽ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ይሁንና የቃሉን ትክክለኛ ጽንሰ ሀሳባዊ ዳራ ለመረዳት መዝገበ ቃላዊ ፍቺውን እንመልከት፤ ‘እምነት’ ለሚለው የእንግሊዘኛ  አቻው ቃል ‘Belief’ ነው፡፡ የኦክስፎርድ እንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት “ስለ አንድ ሰው ወይም አንድ አካል፤ እውነት ነው፣ ጥሩ ነው፣ ትክክል ነው ብሎ በልበ ሙሉነት ሰለነገሩ መናገር ወይም ማመን ነው”(2009፣ 122)፡፡ በማለት ቃሉን ይፈታዋል፡፡ ‘እምነት’ የሚለውን ቃል የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ተቋም የአማርኛ መዝገበ ቃላት ‘ሀይማኖት፣ አምልኮ፣ እርግጠኝነት፣ ሀላፊነት፣ ታማኝነት’ ብሎ ሲፈታው (1993፣ 305)፡፡ ደስታ ተክለወልድ ለቃሉ የሰጡት ፍቺ ቃሉ "ሃይማኖት፣ ማመን፣ መታመን ሲሆን ‘ማመን’ የሚለው ቃል መቀበል፣ መውደድ፣ ማክበር፣ እውነት ነው ብሎ መቀበል

ነው" በማለት ይፈቱታል (1962፣ 108-109) ። የመፅሃፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ደግሞ እምነትን በሁለት መንገዶች ይፈታዋል። የመጀመሪያው፤ "ስለ አምላክ ወይም ስለሰው ዕውቀት ወይም አሳብ" ሁለተኛው "በአምላክ ወይም በሰው ፍፁም ተስፋ ማድረግ" (1962፣ 178) በማለት በይኖታል።

ከብያኔዎቹ መረዳት የሚቻለው 'እምነት' የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ሁለት አካላትን የሚያገናኝ ድልድይ መሆኑን ነው። የመጀመሪያው አንድን ነገር የሚያምነው አካል(ሰው) ሁለተኛው ደግሞ የሚታመነው ነገር (ፈጣሪ፣ ሰው፣ ልዩ ልዩ ሃይላት እና እውነት) ናቸው። ማመን የሚለው ጸናን ጽንሰ ሀሳብ ደግሞ አንድ ነገር ይሆናል ወይም ይፈፀማል ብሎ ማሰብ እንዲሁም አምላክን ወይም ሰዎችን ከጥርጣሬ ነፃ ሆኖ አስተሳሰባቸውን ወይም ድርጊታቸውን መከተል፣ ቸሮታቸውን በተስፋ መጠበቅ ማለት ነው።

የእምነትን ጽንሰ ሀሳባዊ ዳራ በዚህ መልክ ከተመለከትነው ወደ ጥናቱ መዳረሻ ሀገረሰባዊ እምነት እንሻገር። ሀገረሰባዊ እምነቶች (Folk beliefs) በማንኛውም መደበኛ ሃይማኖቶች ውስጥ የማይመደቡ አካባቢያዊና ባህላዊ ገጽታ የሚስተዋልባቸው፤ ሰዎች ስለ አንድ ነገር የሚያምኑባቸውን ኃይላት ወይም ነገሮች እንዲሁም ለማመን የሚፈጽሟቸውን ስርዓቶችና ክዋኔዎች የሚይዝ ጽንሰ ሃሳብ ነው በማለት O'Connor (1995፣15) ይገልጻሉ። Sims እና Stephens በበኩላቸው ሰዎች እንደሚከተሉት እምነት፣ እንደበቀሉበት የማህበረሰብ ባህል፣ እንደየግለሰቦቹ ርዕዮተ ዓለምና እንደሚከተሉት የህይወት ፍልስፍና፣ በቡድንም ሆነ በተናጠል የሚከተሏቸውና የሚከውኗቸው ልዩ ልዩ ሥርዓቶች ሃገረሰባዊ እምነቶች እንደሚባሉ ይገልጻሉ (2005፣ 56-58)። በ O'Connor ፣ Sims እና Stephens ገለጻ መሰረት ሀገረሰባዊ እምነቶች ሀገር በቀል የሆኑና በየትኛውም መደበኛ ሀይማኖቶች ውስጥ የማይካተቱ ፣ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች እንደ አረዳዳቸው በተናጠልም ሆነ በጋራ አንድን ነገር በማመን፣ ላመኑት ኃይል ወይም ነገር ልዩ ልዩ ሥርዓቶችና ክዋኔዎችን እንደሚፈጽሙ መረዳት ይቻላል። ፈቃደ (1991፣14) ሀገረሰባዊ እምነቶችን አስመልክቶ የሚከተለውን ብሏል።

> ሀገረሰባዊ እምነቶች፤ በልዩ ልዩ በዓላት ላይ፣ በመንደር፣ በቤተሰብ፣ በቤተክርስቲያን፣ በመስኪድ፣ በማምለኪያ ስፍራዎች የሚካሄዱትን ክዋኔዎች፤ በልደት፣ በግርዘት፣ በጋብቻ፣ በሞት እና እነዚህን በመሳሰሉ ክዋኔዎች ውስጥ የሚከሰቱ መስተጋብሮችን ያካትታል። የጥናቱ ልዩ ትኩረት ግን ከእነዚህ ጋር የተያያዙ ሀገረሰባዊ እምነቶችን እመመርመር ላይ ነው። በገለጻው መሰረት ሀገረሰባዊ እምነት የአንድ ሀገረሰባዊ እምነት ተከታይ የሆነ ግለሰብ ወይም ቡድን የሚተገብራቸው እምነታዊ ድርጊቶችንና ክዋኔዎችን የሚመለከት ሲሆን የጥናት ትኩረቱም እነዚህን ክዋኔዎች ከተለያዩ ጉዳዮች አኳያ የሚመረምር ነው።

ከዚህ አንጻር በሸካቾ ሀገረሰባዊ እምነት ውስጥ የሁሉ ፍጥረታት የበላይ የሆነ፣ ሁሉን አዋቂ፣ ሁሉ ስፍራ ተገኝና ሁሉን ቻይ የሆነ፣ ግዛቱ የማይወሰን ነገር ግን

ማደሪያውን በሰማያት ያደረገ ፈጣሪ /Yerochi/ እንዳለ ይታመናል[7]። በሸካቾ የእምነት መዋቅር ውስጥ ግዛቱን በሰማያት ያደረገው የሮቺ ከምድራዊው ሰዎች ጋር በአምልኮ አማካኝነት ግንኙነት የሚፈጥርበት ጉዶ ኬሶ የሚባል ቅዱስ ስፍራ አለ። ይህ ቅዱስ ስፍራ ከፍ ያለ ተራራና በደኖች የተከበበ ሲሆን በሁሉም የሸካቾ ጎሳዎች ዘንድ ይገኛል[8]። ይህ ጥናትም በዚህ ቅዱስ ስፍራ ላይ የሚካሄደውን የጉዶ ኬሶ የመስዋዕት በዓል ክዋኔ ይተነትናል።

የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ ትንተና በሸካቾ ብሔረሰብ በሚል የጥናት ርዕሰ ጉዳይን ይዞ ወደ መስክ ስራ ከመወጣቱ በፊትም ሆነ በጥናቱ ሂደት በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ እንዲሁም በሸካቾ ብሔረሰብ ዙሪያ የተጻፉና የተጠኑ ጥናታዊ ጽሁፎችን ለመዳሰስ ተሞክሯል። በብሔረሰቡ ታሪክ ላይ ከተጻፉ ዘለግ ካሉ ታሪካዊ ጽሁፎች ስንጀምር፤ አበራ በጭሮ በ2014 ዓ.ም "የሸካቾ ብሄረሰብ ታሪካዊና የባህል እሴቶች"፣ ወንድም ስሻ አንገሎ በ2013 "እናርያን ፍለጋ" ፣ Warner J. Lange በ1982 G.C "History of the thouther Gonga" በሚል ያሳተሟቸው መጽሀፍት፤ ሸካቾ በታሪክ ሂደት ያሳለፋቸው ውጣ ውረዶች፣ ኬት መጣነት (Genealogy)፣ ልማዳዊ አስተዳደሮች፣ ማህበረ ፖለቲካዊ መዋቅሮች እንዲሁም ከሌሎች የሀገሪቷ ብሄረሰቦች ጋር የነበረራቸውን መስተጋብራዊ ግንኙነት፣ ሶስቱም መጻህፍት አንስተዋል። እነዚህ መጻህፍት ምንም እንኳን የሸካቾን ታሪክ በስፋት ያቀረቡ ቢሆንም ስለ ጉዶ ኬሶ አንስተው ገለጻም ሆነ ትንታኔ ሲሰጡ አልታየም። እርግጥ ነው ወንድምስሻ እናርየን ፍለጋ በሚለው መጽሃፋቸው 'ሀይማኖት ነክ ጉዳችን' (2013፣ 52-64) ባተቱበት ምዕራፋቸው የብሔረሰቡን መደበኛ ሃይማኖቶች በስፋት ሲመለከቱ የሸካቾ ብሔረሰብ ትውፊተዊ እምነቶች እንዳሉት ነገር ግን እነዚህ ሀገረሰባዊ እምነቶች እስካሁን እንዳልተጠኑ ገልጸው "በቀጣይ ቢጠኑ መልካም ይመስለኛል" (2013፣ 62) የሚለው ጥቆማቸው ለዚህ ጥናት አቅጣጫ አመላካች ተደርጎ ይወሰዳል።

በኢትዮጵያ ቋንቋ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍሎች በብሔረሰቡ ባህል ላይ ትኩረት ያደረጉ ጥናቶች ደግሞ፤ ፍጹም ብርሃኑ በ 2006 ዓ.ም "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ"። ምህረት ካሳ በ 2002 ዓ.ም "የ ሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የምግብ ዝግጅት እና የአመጋገብ ስርዓት"። ስለሺ አባተ በ 2002 ዓ.ም "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት"። አማረ ሞላ በ1999 ዓ.ም "የ ሸካቾ ብሔረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና"። ላይ የተደረጉ ናቸው። እነዚህ ጥናቶች በብሔረሰቡ ባህል ላይ መደረጋቸው ከዚህ ጥናት ጋር በቅርበት ያመሳስላቸውል። ይሁን እንጂ በአምልኮ ስፍራዎች ላይ የሚፈጸሙ እምነት ነክ ክዋኔዎችን ጉዳያቸው አድርገው አልዳሰሱም፤ አልተነተኑም። በጥቅሉ የዚህን ጥናት ርዕሰ ጉደይ በጥናታቸው አላመላከቱም።

ከአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ውጪ ደግሞ አውግቸው ወርቅአገኘሁ በ1989 ዓ.ም "ትውፊትና ባህላዊ ክንዋኔዎች በሸካ ብሔር" በሚል

[7] ቃ.መ. አበራ በጭሮ 09/08/2014 ዓ.ም

[8] ቃ.መ. ዳንበራኖ አለሙ ሸኖ 11/08/2014 ዓ.ም

ለትያትር ትምህርት ክፍል ያቀረቡት የመመረቂያ ጽሁፍ ለዚህ ጥናት ከቀረቡ መመረቂያ ጥናቶች በተሻለ ቀረብ ያለ ይመስላል። አውግቸው ብሔረሰቡ ላይ ትኩረት አድርገው የብሔረሰቡን ሃገረሰባዊ ትውን ጥበባት (Performing folk art) እና ትውፊታዊ ክዋኔዎችን ዘርዝረዋል። ከዘረዘሯቸው ትውፊታዊ ክዋኔዎች መካከል ደግሞ  የጉዶ ኬሶ ክዋኔ ይገኛል። ይሁንና ይህ ክዋኔ በአውግቸው ጥናት ውስጥ ገለጻና ትንተና ስላልቀረበበት ምልዑነት ይጎድለዋል።

Getaneh Haile በ 2022, "The contribution of Gudo forest conservation culture is key to biodiversity conservation the case of Sheka Zone, southwest Ethiopia" በሚል ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ በሸካቾ ብሔረሰብ እና በጉዶ ባህል ላይ ተወስኖ መቅረቡ ለዚህ ጥናት ከሌሎች ጥናቶች በተለየ ይቀርበዋል፡ ፡ የጌታነህ የጥናት ትኩረት የጉዶ ደን እና በደኑ ዙሪያ የሚገኙ የብዝሃ ህይወት ሀብቶች መጠበቅ ምክንያቶችን እመፈለግ ላይ የተወሰነ ነው። ጥናቱ በጉዶ ደኖች አካባቢ የተለያዩ የብዝሀ ሕይወት ሀብቶች እስከዛሬ ተጠብቀው የዘለቁት የጉዶ ባህል መኖሩ እንደሆነ ይጠቁማል። ጌታነህ መረጃን ለመተንተን ገላጭ የስታቲስቲክስ ዘዴዎች ጥቅም ላይ አውሏል። መረጃዎን ለመሰብሰብ ደግሞ ቃለ መጠይቅ እና የተተካሪ ቡድን ውይይትን አካሂዷል። ይሁንና የጉዶ ሀገረሰባዊ እምነት እንዴት ይከወናል? የክዋኔው ሂደት ምን ይመስላል? በክዋኔው ላይ የሚቀርቡ ቴክስቶች፣ ቁሶችና ድርጊቶች ምን ትዕምርት (Symbol) አላቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ባለመስጠቱና ክዋኔውን በምልከታ ባለማረጋገጡ ከዚህ ጥናት ጋር በእጅጉ ይለያል። ይህ ጥናትም የጌታነህን የጥናት ክፍተቶች በመሙላቱ ረገድ ከፍ ያለ ሚና ይጫወታል።

በአጠቃላይ በብሄረሰቡ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ትኩረታቸው፤ በሸካቾ ተረቶች፣ ባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት እና የአመጋገብ ስርዓቶች፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት፣ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት፣ ሀገረሰበዊ ትውን ጥበባት፣ እና የጉዶ ባህል ለአካባቢ ብዝሃ ህይወት መጠበቅ በሚያበረክተው ፋይዳ ላይ የተደረጉ ናቸው። እስካሁን በተደረገው የቤተመጻህፍትና የወመዘክር እንዲሁም የኢ-ላይብረሪ ፍተሻ "በጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ" ላይ በቀጥታ ትኩረት ያደረገ ምርምር ማግኘት አልተቻለም[9]። ከዚህ

---

[9] በዚህ ዳሰሳ ውስጥ ያልተካተቱ ጉዳያቸውን በሸካቾ ብሔረሰብ ላይ ያደረጉ ነገር ግን ከዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው ሰባት ጥናቶች ማጣቀስ ለሚፈልጉ መረጃ ይሆን ዘንድ እንምደሚከተለው ቀርበዋል፤ Wasihun Bekele and Admasu Adraro በ 2022 "Ethiopia: Indigenous Conflict Resolution Mechanism of Shekacho people and its role in Promoting Peace and Good Governance." Zewdie Kassa Tessema, Zemede Asfaw and Sebsebe Demissew በ 2020 "Ethno-ecological study of medicinal and wild edible plants in Sheka Zone" Getaneh Haile በ 2020 "The DEDO Forest Conservation Culture a Means to Conserves the Ororo (Ekebergia Capensis) Tree." Behailu Ayele በ 2016 "Exploration into Co-Cultural communication between Manjo and donjo in Sheka". Matthias De Beenhouwer, Bernard Oosterlynck and Mattias Van Opstal በ 2016 "Express Biodiversity Survey in Sheka Forest Biosphere Reserve, Ethiopia" Workaferahu Ameneshewa በ 2015 "Spatio-Temporal Forest Cover Change Detection Using Remote Sensing and GIS Techniques: In the case of Masha

የተነሳ "የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ ትንተና በሸካቾ ብሔረሰብ" የሚለው ርዕሰ ጉዳይ መጠናቱ በመስኩ ያለውን ሰፊ የእውቀት ክፍተት ይሞላል፡፡

"ጉዶ ኬሶ ፈጣሪ የሰው ልጆችን ሁለንተና ለማስተካከል መጀመሪያ የመረጠው የተቀደሰ ተራራ ነው"[10]፡፡ በዚህ ተራራ ላይ ደግሞ የሸካቾ ጎሳዎች በሰባት ዓመት አንድ ጊዜ ለፈጣሪ(ለሮቺ) ታላቅ የሚባለውን መስዋዕት በማቅረብ አምልኮ ይፈጽማሉ[11]፡፡ የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዋና ዓላማም ይኸው ለየሮቺ በተራራ ላይ የሚቀርበውን "የጉዶ ኬሶ ሀገረሰበዊ እምነት ክዋኔ መተንተን" ነው፡፡ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት፤ የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ስርዓት ክዋኔ ሂደት ምን ይመስለል? በጉዶ ክዋኔ ወቅት የሚቀርቡ ቴክስቶች፣ ቁሶችና ድርጊቶች ምን አይነት ትዕምርት አላቸው? የጉዶ ኬሶ ክዋኔ በመከወኑ የሚገኘው ጥቅምና ባይከወን ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ምንድን ነው? የሚሉ መሪ የምርምር ጥያቄዎች ተነስተው በጥናታዊ ጽሁፉ መልስ ያገኛሉ፡፡

## 1.1. የሸካቾ ብሄረሰብ አካበቢያዊና ማህበራዊ ዳራ

የሸካቾ ብሔረሰብ በደቡብ ምዕራብ ክልላዊ መንግስት በሸካ ዞን ውስጥ ከሚገኙ ነባር ብሔረሰቦች አንዱ ነው፡፡ የብሔረሰቡ አባላት በዋናነት በዞኑ በሚገኙ 3 ወረዳዎች በማሻ፣ በየኪ እና በአንድራቻ ወረዳዎች በስፋት ሰፍረው የሚኖሩ ሲሆን ከዞኑ ውጪ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በኢሉባቡር ዞን በሰሌ እና ኖኖ ወረዳዎች እንዲሁም በጋምቤላ ብሔራዊ ክልል መንግስት በጎደሬ ወረዳ ዉስጥም ይገኛሉ፡፡ የዞኑ ዋና ከተማ ማሻ ስትሆን ከ15¸000 ሕዝብ በላይ ይኖርባታል፡፡ ማሻ ከአ/አ 680 ኪ/ሜ ትርቃለች፡፡ ዞኑ በሰሜን ከኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ከቤንች ማጂ ዞን፣ በምሥራቅ ከከፋ ዞን፣ በምዕራብ ከጋምቤላ ክልል የሚዋሰን 2,175.26 ስኩዌር ኪ.ሜ የቆዳ ስፋት አለው (የሸካቾ ዞን ፕላን መምሪያ ዓመታዊ ዕቅድ 2014፣ 22)፡፡

በማዕከላዋ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የህዝብና የቤቶች ቆጠራ የሕዝብ ብዛት ትንበያ መሰረት የሸካ ዞን ሕዝብ በ2007 ዓ.ም 199,314 ይደርሳል፡፡ ከዚህም ውስጥ 165,087 (82.5%) የሚሆነው ሕዝብ የገጠር ነዋሪ ሲሆን 34,227 (17.5%) ደግሞ በከተማ እንደሚኖር ግምቱ ያሣያል (2007፣24-26) ፡፡

በደቡብ ክልላዊ መንግስት ፕሮፋይል መሰረት የሸካቾ ብሄረሰብ ከዞኑ ጠቅላላ ሕዝብ የሚሆነው 67.76 ከመቶው የክርስትና ሃይማኖትን ሲከተሉ 13.9 በመቶው የእስልምና፣ 17.8 በመቶው የሀገረሰባዊ እምነት ተከታዮች ናቸው፣ 0.54 በመቶ ደግሞ የሌላ እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡ የብሔረሰቡ ቋንቋ "ሸክኖኖ" በመባል

Woreda, Sheka Zone, SNNPRS, Ethiopia". Workaferahu, Yechale, Dakiso and Abyot በ 2013 "Indigenous Forest Management of the Shakicho people in which they explained the belief system." በሚል የተካሄዱ ናቸው፡፡

[10] ቃ.መ. ወልታታ ባህሩ ወ/ጊዮርጊስ 18/09/2014 ዓ.ም፣ ቃ.መ. ዳንበራኖ አለሙ 11/08/2014 ዓ.ም

[11] ቡ.ው አቴስታታ ዳኬቶ መጅቶ፣ አቶ ዘውዴ ግችላ፣ ዳምበራኖ አለሙ ሸኖ፣ ኦጎ ንገራሻ፣ ታምሩ ኮቶ፣ ወልታታ ባህሩ ወ/ጊዮርጊስ፣ አምባሳደር አበራ በጭሮ፣ ወ/ሮ አሰገደች ሽታኖ ፣ንፈራሻ እሸቱ፣ አቶ ፍቃዱ አውዶ፣ ቆመ ቆጭቶ 29/09/2014ዓ.ም

ሲታወቅ ከኦሞአዊ ቋንቋዎች ቤተሰብ የሚመደብ ነው፡፡ ቋንቋው ከካፈቾ ቋንቋ "ካፊኖኖ" ጋር የመመሳሰልና የመቀራረብ ባህርይ ስላለው የሁለቱም ብሔረሰቦች አባላት በቋንቋቸው እርስ በርስ ያለ አስተርጓሚ ይግባባሉ (2001፣11-112)::

የሸካቾ ብሔረሰብ በራዶ እና አካኮ በመባል በሚታወቁ ሁለት ጎሳዎች (የዘር ግንዶች) የሚከፈል ሲሆን በእያንዳንዱ ሥር የታቀፉ በርካታ ጎሣዎች እንዲሁም በእያንዳንዱ ጎሣ ሥር የተለያየ ስያሜ ያላቸው በርካታ ንዑሳን ጎሳዎች አሉት፡፡ ብሔረሰቡ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ ይዞት የመጣው የራሱ የሆነ ባህላዊ አስተዳደር አለው፡፡ ባህላዊ አስተዳደሩ በንጉስ/ታቶ/ ይመራል፡፡ የንጉሡ ሥልጣን በዘር ሐረግ የሚተላለፍ ሆኖ ከባራዶ ማህበራዊ መደብ ከቡሻሾ ጎሣ ይመረጣል[12]፡፡ ከንጉሡ/ታቶ/ በታች ‹‹ካተራሻ›› የሚባል የባህላዊ አስተዳደር መዋቅር አለ፡፡"ካተራሻ" ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ ችሎታውንና እውቀቱን መሠረት በማድረግ የመስቀል በዓል በሚከበርበት ዕለት በህዝብ ምርጫ ይመረጣል፡፡ ዋና ተግባሩ /የጦር አዛዥ/ የሆነው "ወላሻ" ደግሞ ከካራዶ ማህበራዊ ቡድን /ጎሣ/ ይመረጣል፡፡ ተግባሩም 12 የጐሣ መሪዎችን በበላይነት መምራትና ጦሩን በበላይነት ማዘዝ ነው፡፡ በብሔረሰቡ ባህላዊ አስተዳደር ውስጥ ካከተራሻ ጋር ስምንት አባላት ያሉት የአማካሪ ምክር ቤት አለ፡፡ ምክር ቤቱ "ምክራቾ" ይባላል፡፡ ሰባቱ የምክር ቤት አባላት አካከራሻ፣ወላሻ፣ ጨተራሻ፣ ሺሸራሻ፣ ፋራሻ ፣ታታቡሻ እና ሾራሻ የሚባሉ ንጉሡን የሚያማክሩ የምክር ቤት አባላት ናቸው፡፡ የንጉስ /ታቶ/፤ ቤተመንግስት/ጭዶ/ በአንድራቻ ወረዳ ከጌጫ ከተማ ከፍ ብሎ በሚገኘው ተራራማ ቦታ ላይ ነው (የደቡብ ክልላዊ መንግስት ፕሮፋይል፣112)፡፡

## 2. የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ ማሕቀፎች

በዚህ ጥናት ከመስክ የሚገኙ መረጃዎች በክዋኔ መር (Performance Theory) እና በትዕምርት ንድፈ ሀሳባዊ (Symbolic Theory) ማሕቀፎች አማካኝነት የሚፈከሩ ይሆናል፡፡የክዋኔ መር ንደፈ ሀሳብ የእምነት ክዋኔዎችን ለማጥናት አመቺ ንድፈሃሳብ በመሆኑ በዘመናችን ተቀባይነት እያገኘ እንደመጣ Atkinson (2004፣ 109) ይገልጻሉ፡፡ የክዋኔ መር ንድፈ ሃሳብ በዋናነት ትኩረት የሚያደርገው፤ ድርጊቱን ማን ፈጸመው? ምን ተፈፀመ? ለምን ተፈፀመ? ድርጊቱ ለማን ቀረበ? መቼና የት ተፈፀመ ? እንዴት ተፈፀመ? በሚሉ ዋና ዋና የክዋኔ ገጽታዎች ላይ ነው Bauman (1975፣ 299)፡፡ እንደ Bauman አገላለፅ፤ የክዋኔ ገጽታዎቹ፤ ክዋኔው የተፈፀመበትን ቦታና ጊዜ ፣ የክዋኔውን ሥርዓተ ሂደት፣ የተሳታፊዎችን ሁኔታ፣ የከዋኙን የአከዋወን ስልት፣ ሥርዓተ ክዋኔውን ይመለከቱ የነበሩ ግለሰቦች ለክዋኔው የነበራቸውን ስሜት፣ ሥርዓተ ክዋኔው የተካሄደበትን የጊዜም ሆነ የአከዋወን ቅደም ተከተል እና የክዋኔውን ተግባር የሚያካትቱ ናቸው፡፡ ከዚህ የክዋኔ ንድፈ ሀሳባዊ ሀቲት በመነሳት የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ ተፈክሯል፡፡

[12] ቃ.መ ሰራዊት ሸሎ፣ ኦሳ ንገራሻ፣ ወልታታ ባህሩ 07/09/2014)

ከዚህ በተጨማሪም ጥናቱ በክዋኔ ላይ የሚታዩ ቴክስቶች፣ ቁሶችና ድርጊቶች ተምሳሌታዊ ትርጉማቸውን ተረድቶ መፈከር ያስችል ዘንድ ተምሳሌታዊ ንድፈ ሀሳብን ተጠቅሟል፡፡ Cooke እና Macy ከበራና ትዕምርት ያላቸውን ጥምረት ሲገልጹ፤ "ትዕምርት የከበራዎች መሰረት ነው፡፡ ትዕምርት የሌለባቸው ሥርዓተ ከበራዎች የሉም (2005፣ 14) ፡፡ በማለት ትዕምርት እና ከበራዎች ያላቸው ጥምረት ምን ያህል ከፍ ያለ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ መሰረታዊ የንድፈ ሃሳብ ሀቲት በመነሳት በጉዶ ኬሶ ክዋኔ ወቅት የሚከወኑ ክዋኔዎች ያላቸው የክወና ቅደም ተከተል፣ ከዋኞቹ የሚጠቀሟቸው ቁሳዊ ባህሎች ያላቸው ውክልና፣ ግለሰቦች ያላቸው ማህበራዊና ባህላዊ ውክልና፣ የሚቀርቡ ክወናዎች የሚፈጥሩት የእርስበርስ ተግባቦትና የሚያሳዩት የኃይል መስተጋብር፣ በጥናቱ ትርጉም እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡

## 3. የጥናቱ ስነ ዘዴዎች

ከዚህ ጥናት ዓላማ፣ ከሚሰበሰቡ የመረጃ አይነቶች፣ ከአተናተን ዘዴዎችና በአጠቃላይም ከምርምር አካሄዱ አኳያ ጥናቱ አይነታዊ ምርምር ነው፡፡ ዓይነታዊ ምርምር አንድ ጉዳይ ምን እንደሚመስል ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት አድርጎ በገለፃና በሃተታ መልክ በማቅረብ ስለነገሩ ምንነትና ትክክለኛ ባህሪ ሰፊና የዳበረ ማብራሪያ የሚሰጥበት ነው Jupp (206፣ 248 - 249) ፤ Kothari (1985፣ 3)፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ የምርምር ዓይነት ውስን አካባቢን፣ ውስን መረጃ ሰጭዎችንና ውስን መረጃዎችን በመውሰድ የሚጠናውን ርዕሰ ጉዳይ በስፋት፣ በጥልቀትና በዝርዝር የሚፈትሽ ነው፡፡

ከጥናቱ አይነትና ባህሪ በመነሳት መረጃ ሰጪዎችን ለመምረጥ ጥቅም ላይ የዋለው ዘዴ ደግሞ ዓላማ ተኮር ንሞና (Purposive Sampling) ነው፡፡ ይህን ዘዴ በመጠቀም ለዚህ ጥናት ተስማሚ የሆኑ ሁለት የንሞና ስልቶች ተመርጠዋል፡፡ የመጀመሪያው ዓይነተኛ ንጥል ንሞና (Typical-case Sampling) ሲሆን ይህንን የንሞና ዓይነት በመጠቀም የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ ተጠንቷል፤ በዚህ ንሞና የአቴሶ ጎሳ መሪን ጨምሮ በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ አራት፣ ከሌሎች ሰባት ቀበሌዎች ደግሞ ሰባት በድምሩ 11 ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ተመርጠዋል፡፡ ከአቴሶ ቀበሌ ውጪ ካሉ ሰባት ቀበሌዎች ደግሞ 16 ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮችን በድምሩ 27 መረጃ አቀባዮች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ የአቴሶ ጎሳ መሪ የሆኑት አቴስታታ ዳኬቶ ለቃለ መጠይቁም ሆነ በእርሳቸው የጉዶ ደን አካባቢ ጥናቱ እንዲደረግ የተመረጠበት ምክንያት አሁንም ድረስ የጉዶን የመስዋዕት አቅርቦት ክዋኔ እየፈጸሙ በመገኘታቸው ነው፤ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በዕድሜ ከሌሎቹ ጎሳ መሪዎች ገፋ ያሉ በመሆናቸው ከስልሳ ዓመታት በፊት አያታቸው ጉዶን ሲያከብሩ እየተመለከቱ በማደጋቸው ምክንያት ነው፡፡ ይህም አሁን ያለውን የጉዶ ኬሶ ክዋኔ ብቻ ሳይሆን የጉዶን ለውጥና ቀጣይነት ለማጥናት እርሳቸውና በእርሳቸው ዙሪያ ያሉ የባህል መሪዎች በቂ የሆነ መረጃ እንደሚሰጡ በዚህ ጽሁፍ አቅራቢዎችም እና በብሔረሰቡ የጎሳ መሪዎች በመታመኑ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ከአቴሶ ቀበሌ አቴስታታ ዳኬቶን ጨምሮ አራት (ሶስት ወንድ እና አንድ ሴት)፣ ከሌሎች ሰባት

ቀበሌዎች ደግሞ ሰባት (አራት ወንድ እና ሶስት ሴቶች) በድምሩ 11 ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ተመርጠዋል፡፡ ከሌሎች ሰባት ቀበሌዎች 16 (ስምንት ወንድ እና ስምንት ሴቶች) ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች በድምሩ 27 መረጃ አቀባዮች ተመርጠው ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

ሁለተኛው ጠቋሚ ወይም ተያያዥ ንሞና (Network or Snowball Sampling) ነው፡፡ ይህ ዘዴ መረጃ ሰጪዎች ለአጥኚው በሚሰጡት ጥቆማ መሰረት መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ግለሰቦች የሚመረጡበት ነው፡፡ ይህን የንሞና ዓይነት በመጠቀም የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ ምልከታ ከተደረገ በኂላ በዓይነተኛ ንጥል ንሞና ወቅት በቁልፍ መረጃ አቀባዮች ጠቋሚነት ሶስት (ሁለት ወንዶች እና አንድ ሴት) ተጨማሪ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ተለይተዋል፡፡

የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ሥርዓተ ክዋኔ በአቴሶ[13] ቀበሌ "ጋበዮቺ ጉዶ" ቅንብር ተፈጥራዊ መቼት (Induced Natural Setting)[14]ን በማዘጋጀት ሚያዝያ 23 ቀን 2014 ዓ.ም ምልከታ ተካሂዷል፡፡ በዚህ ጥናት ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃዎችን ከመስክ ለመሰብሰብ ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

ጥናቱ የተሳትፎ እና የኢ-ተሳትፋዊ ምልከታን የተገበረ ሲሆን፤ ተሳትፏዊ ምልከታን ጥብቅ ቀኖናዊ ህጎች በሌሉባቸው የክዋኔው ሁነቶች ውስጥ እንደተሳታፊ በመቅረብ፤ የጉዶ መስዋዕት በሚቀርብበት ሚስጥራዊ ስፍራ ደግሞ ኢ-ተሳትፋዊ ምልከታ በማድረግ መረጃ መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ከየካቲት 3 እስከ ሰኔ 26 ቀን 2014 ዓ.ም በተጠኝ ማህበረሰብ ውስጥ በመቆየትም ስለ ክዋኔው ጠለቅ ያለ እውቀት ማግኘት ተችሏል፡፡

በሁለተኛነት ክፍት (Open Ended) ቃለ መጠይቅ እና ዝግ (Close Ended) ቃለ መጠይቆች በጥናቱ ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ ዝግ ቃለ መጠይቅ ተግባራዊ የተደረገው ስለህብረተሰቡ አጠቃላይ መረጃ ለማግኘት ሲሆን ክፍት ቃለ መጠይቅ ደግሞ የመከወኛ አጋጣሚ ዳራዎቹንና የክዋኔ ሁነቶችን ቀድሞ ለመረዳት፣ ክዋኔዎቹ እንዴት፣ ለምንና እና መቼ፣ በዚህ መልክ መከወን እንደተጀመሩ ለማወቅ፣ በክዋኔ ላይ የሚቀርቡ ስነ ቃሎችን መልሶ ለማዋቀር፣ በማህበሩ ውስጥ በሚኖሩ ልዩነቶች ሳቢያ የአከዋወን ስርዓቶቹ የሚለያዩ መሆን እና አለመሆናቸውን ለማስረገጥ፣ ክዋኔዎቹ በዚህ መልክ መከወናቸው ለማህበሩ ያስገኛል ተብሎ ስለሚታሰበው

---

13 የአቴሶ ቀበሌ ለቅንብር ተፈጥራዊ መቼቱ የተመረጠው፡፡ በ19/07/13 ዓ.ም ከሸካቾ ጎሳ መሪዎችና የሀገር ሽማግሌዎች ጋር በማሻ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ውስጥ በተደረገ ስምምነት ነው፡፡ የስምምነቱ ማዕከላዊ ጉዳይና መደምደሚያ የጉዶ ኬሶ በዓልም ሆነ ሌሎች ሀገረሰባዊ እምነቶች አሁንም ድረስ ብዙ ሳይበረዙ እየተከወኑ የዘለቁበት ቀበሌ አቴሶ በመሆኑ የክዋኔዎቹ የጥናት መነሻ አቴሶ ቀበሌ ይሁን የሚል ነበር፡፡

14 ይህም የሆነው የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት አንድም በየሰባት አመቱ አንድ ጊዜ ብቻ ስለሚከበርና ሰባት ዓመትን ጠብቆ ማጥናት ጊዜ በመፍጀቱ ነው፡፡ ሁለትም በተፈጥራዊ መቼቱ ላይ መገኘት ቢቻል እንኳን የእምነቱን ጥብቅ ዶግማዊና ቀኖናዊ ህግጋት መጠበቅን ግድ ስለሚል ነው፡፡ ሶስተኛው ምክንያት ደግሞ አሁን አሁን የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት በመደበኛ እምነቶች ጫና የተነሳ በውስን የባህል መሪዎችና ቤተሰቦቻቸው አማካኝነት ብቻ የሚከበር በመሆኑ ክዋኔው በሚስጥር ስለሚያዝ ነው፡፡

ፋይዳ፣ በክዋኔዎቹ ስለሚስተዋሉ ቁሳዊ ባህሎች፣ ቴክስቶች እና የአካላዊ እንቅስቃሴዎችን ትርጉም ለማግኘት ነው፡፡ ለቃለ መጠይቁ የተመረጡ ሰዎች በሶስት ጎራ ተመድበዋል፤ እነዚህም ክዋኔዎቹን የሚመሩ ከዋኞች፣ በክዋኔዎቹ ቀጥተኛ ተሳታፊ የሆኑ ታዳሚዎች፣ ባህሉን በሚገባ የሚያውቁ የአካባቢው ነዋሪዎች እና የባህል ባለሙያዎች ናቸው፡፡

በሶስተኛነት ጥቅም ላይ የዋለው መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ነው፡፡ የተተኳሪ ቡድን ውይይት በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ወቅት ግልጽ ያልሆኑ መረጃዎችን ለማጥራት፣ ትርጉም የሚያስፈልጋቸውን መረጃዎች ትርጉም ለመስጠት እንዲሁም የመረጃዎቹን ጥራት ለመመዘን ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የተተኳሪ ቡድን ውይይቱ በአንድ ቡድን የተዋቀረ እና ስምንት (አምስት ወንዶች እና ሶስት ሴቶች) ተወያይ ያሉበት ነው፡፡ ከሙያ ተዋጽኦ አንጻር፤ (ሶስት ወንድ) በእድሜ ገፋ ያሉ የሀገረሰባዊ እምነቱ መሪዎች፣ ሁለት (አንድ ወንድ እና አንድ ሴት) ከዋኞች፣ ሁለት ወንድ የባህል ባለሙያዎች፣ በብሔረሰቡ ማህበራዊና ታሪካዊ ሁነት ላይ ጥልቅ እውቀት የነበራቸው ሁለት የብሄረሰቡ ተወላጆች ተመርጠው ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

ከምልከታ፣ ከቃለ መጠይቅና ከተተኳሪ ቡድን ውይይት የተገኙ መረጃዎችን ለመተንተን ደግሞ ጥናቱ ገላጭ (Descriptive) የመረጃ መተንተኛ ዘዴን ተከትሏል።

## 4. የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ሥርዓተ ክዋኔ ትንተና

የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ የሸካቾ ብሔረሰብ በሰባት ዓመት አንድ ጊዜ አስቀድሞ ለዚሁ ከበራ በተለየ ቅዱስ ተራራ ላይ ለየሮቺ መስዋዕት በማቅረብ የሚያከብሩት የመባ እና የምስጋና በዓል ነው፡፡ ጉዶ ኬሶ ከሸካቾ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔዎች መካከል ትልቅ ክብር የሚሰጠውና ዋናው የመስዋዕት በዓል ሲሆን በዓሉን በሸካቾ ብሔረሰብ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ጎሳዎች በየጎሳቸው ቀን ቆርጠውለት በሰባት ዓመት አንድ ግዜ ብቻ ፈጣሪ (የሮቺ) ስላደረገላቸው መልካም ነገር፣ ስለሰጣቸው በረከት፣ ስላሰፈነላቸው ሰላም፣ ስለሰጣቸው ጤና፣ ስላስጠበቀላቸው መልካም ስነምህዳር፤ ሲሉ ከፍ ባለ ተራራ ላይ በመገኘት[15] የሚያከብሩት የመስዋዕት ወይም የመባ በዓል ነው፡፡

[15] በዚህ ዘመን የሚከበሩ የጉዶ ኬሶ በዓላት በአብዛኛው በጎሳ መሪው ቤተሰቦች እና ጥቂት ባለሚሎች እንዲሁም ጥብቅ የሆነውን የመንጻት ስርዓት በፈጸሙ የብሄረሰቡ አባላት አማካኝነት ነው፡፡ አሁን አሁን በአንድ ጉዶ ላይ የሚገኘው ታዳሚ ቢበዛ ከ300 አይልቅም፡፡ ይህም ቢሆን ከበራው በሚስጥር እንጂ በይፋ አይከወንም፤ ለዚህ ሁለት ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። የመጀመሪያው ምክንያት የኦርቶዶክስና የፕሮቴስታንት ሃይማኖቶች መስፋፋታ እና የትውፊታዊ እምነት ተከታዮችን የማግለል ዝንባሌ እየተስተዋለ ስለመጣ ነው፡፡ የአማኞቹ ቁጥር ከዕለት ዕለት እየቀነሰ የመጣበት ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የጎሳው አባላት የእምነቱን ጥብቅ ቀኖናዎች በመፍራት እና በትክክል ካልከወንን መቅሰፍት ወደቤታቸን ይገባል በሚል ስጋት ነው፡፡ ከ1966 ዓ.ም በፊት ግን ጉዶ ላይ ተገኝቶ የሚያከብረው ታዳሚ ቁጥር ከ6000 ቢልቅ እንጂ አያንስም ነበር፡፡ (ቃ.መ፤ ወልታታ ባህሩ ወ/ጊዮርጊስ 09/08/14 ዓ.ም)፡፡

የሸካቾ ብሔረሰብ ይህንን የጉዶ ኬሶ የመስዋዕት ሥርዓተ ክዋኔ በየጎሳቸው ስያሜ ሰጥተው ያከብሩታል፡፡ በአቴሶ ጎሳ "ጋቦዮቺ ጉዶ" በወሎጎሳ "ዳኮቺ ጉዶ" በአበሎ ጎሳ ደግሞ "ጋኮቺ ጉዶ" በሌሎቹም የሸካቾ ጎሳዎች እንዲሁ ስያሜ ሰጥተው ያከብሩታ[16]።

እንደ ብሔረሰቡ የጎሳ መሪዎች ገለጻ በሸካቾ ብሔረሰብ የጉዶ ኬሶ ሥርዓተ ክዋኔ መከወን የተጀመረው ብሔረሰቡ በንጉስ ሰለሞን ዘመነ መንግስት ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ ሲፈልስ በርከት ያሉ ኦሪታዊ ክዋኔዎችን ይዞ መጥቷል፡፡ ይዞ ከመጣቸው ኦሪታዊ ክዋኔዎች መካከል ደግሞ አንዱ እስራኤላውያን ለአምላካቸው በተራራ ላይ የሚያቀርቡትን የመስዋዕት ሥርዓተ ክዋኔ ነው፡፡ የጉዶ ኬሶ የመስዋዕት በዓል በሸካቾ ብሔረሰብ የሚከበረውም አብርሃም ለፈጣሪው ያቀርብ የነበረውን የተራራ ላይ መስዋዕት (ዘፍ. 22፡13) በማስታወስ ነው[17]፡፡

የሸካቾ ብሔረሰብ ከክርስቶስ ልደት በፊት የጉዶ ኬሶን ክዋኔ ከታህሳስ ወይም ከጥር ወራት አንዱን በመምረጥ ያከብር እንደነበር የጎሳ መሪዎቹ ይናገራሉ[18]፡፡ እነዚህ ወራቶች ምርት የሚሰበሰብባቸውና እህል ወደ ጎተራ የሚከማችባቸው ወቅቶች በመሆናቸው ብሔረሰቡ በኩር(የመጀመሪያ) የሆነውን ምርት ለየሮቺ እየሰዋ ጉዶ ኬሶን ያከብር ነበር፡፡ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ግን አብዛኛው የሸካቾ ብሔረሰብ የክርስትናን እምነት በመቀበሉ ምክንያት የጉዶ ኬሶ ሥርዓተ ክዋኔን ከዓብይ ጾም ጋር በማገናኘት ማክበር ጀመረ፡፡ ይህ የሆነበት ዋና ምክንያት በብሉዩ ዘመን የጉዶ ኬሶ ሥርዓተ ክዋኔን የሚያስፈጽሙ የጎሳ መሪዎች በዓሉን ከማክበራቸው በፊት አርባ ቀን ከሰው ተለይተው በተዘጋጀላቸው ጎጆ ጾም ጸሎት ይገቡ ነበር[19]፡፡ ነገር ግን ብሔረሰቡ ክርስትናን ከመቀበሉ ጋር ተያይዞ የዓብይ ጾምን አርባ ቀን መጾም ሲጀምር የጎሳ መሪዎቹ ተመካክረው በዓመት ሁለት ጊዜ አርባ ቀን የሚጾመውን ጾም ላለመድገም የአብይ ጾምን ብቻ በመጾም የጉዶ ኬሶ ሥርዓተ ክዋኔን ማክበር እንደሚቻል እያመኑበት መጡ፤ ከዛን ጊዜ ጀምሮ ነው የጉዶ ኬሶ ሥርዓተ ክዋኔ ከትንሳዔ በዓል እስከ በዓለ ሃምሳ ባሉት ቀናቶች ውስጥ መከበር የጀመረው[20]፡፡

በብሉይም ሆነ በዘመነ ክርስትና የጉዶ ኬሶ ሥርዓተ ክዋኔ የሚከበረው በሰባት አመት አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ሰባተኛው ዓመት ተጀመሮ እስኪያልቅ ድረስ ምንም ስራ አይሰራበትም፡፡ ዓመቱ በሙሉ የበዓሉ አንድ አካል በመሆኑ ብሔረሰቡ ስድስቱን ዓመታት ያከማቸውን ምርት ከጎተራ እያወጣ ነው የሚመገበው፤ ከብቶች እንኳን

---

[16] ቃ.መ ዳንበራኖ አለሙ ሸኖ 19/08/14 ዓ.ም

[17] ቡ.ው አቴስታታ ዳኬቶ፣ ዘውዴ ግችላ፣ ዳምበራኖ አለሙ፣ ኦጎ ንገራሻ፣ ታምሩ ኮቶ፣ ወልታታ ባህሩ፣ አምባሳደር አበራ በጭሮ፣ ወ/ሮ አሰገደች ሽታኖ ፣ንፈራሻ እሸቱ፣ፍቃዱ አውዶ፣ ቆመ ቆጭቶ 29/09/2014 ዓ.ም

[18] ቃ.መ ወልታታ ባህሩ ወ/ጊዮርጊስ 19/08/14 ዓ.ም

[19] ቃ.መ ዳንበራኖ አለሙ ሸኖ 19/08/14 ዓ.ም

[20] ቡ.ው አቴስታታ ዳኬቶ፣ ዘውዴ ግችላ፣ ዳምበራኖ አለሙ፣ ኦጎ ንገራሻ፣ ታምሩ ኮቶ፣ ወልታታ ባህሩ፣ አምባሳደር አበራ በጭሮ፣ ወ/ሮ አሰገደች ሽታኖ ፣ንፈራሻ እሸቱ፣ፍቃዱ አውዶ፣ ቆመ ቆጭቶ 29/09/2014 ዓ.ም

የመሬቱን ሳሩ እንዲግጡ አይደረግም[21]:: ሰባተኛው ዓመት የተመረጠበት ምክንያት ፈጣሪ(የሮቺ) መሬቱን ከማረስና ምርት ከመሰብሰብ አሳርፈን እንድናመልከው ስላዘዘ ነው፤ ይህም በብሉይ መጻህፍት ውስጥ ተገልጿል[22]በማለት የጎሳ መሪዎቹ ይገልጻሉ:: አይሁዳውያን በሙሴ ህግ መሰረት የሚያርሱትን ምድር ሰባተኛው ዓመት ላይ እንደሚያሳርፉ ሁሉ (ዘሌዋ. 25:2-8 ፤ 26:34-35 - 2ኛ ዜና. 36: 21) የሸካቾ ብሔረሰብም እንዲሁ ሰባተኛውን አመት መሬቱን ያሳርፋል፤ አያርስም፣ አይዘራም፣ አያጭድም::

በመቀጠል የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ሥርዓተ ክዋኔ ከቅድመ ዝግጅቱ እስከ በዓሉ ማግስት ድረስ ያለው የአከዋወን ሂደት በቅደም ተከተል ይቀርባል::

### 4.1. የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ ቅድመ ዝግጅቶች

የጉዶ ኬሶ ክዋኔ አጠቃላይ ቅድመ ዝግጅት የሚጀምረው ከሶስት ወራት ቀደም ብሎ ነው:: የጉዶ ኬሶ ክዋኔ ዕለተ ቀኑ ከተወሰነለት ጊዜ አንስቶ በጎሳ መሪው አማካኝነት የበዓሉ አስተባባሪዎች ይመረጣሉ:: ነባሮቹ የቀድሞ አስተባባሪዎች በህይወት ካሉ እነሱኑ ዳግም ጎሳ መሪው ሊያደራጇቸው ይችላሉ:: ምርጫው በጎሳ አባላት ዘንድ ያለ ተቀባይነትን ያገናዘበ ሲሆን አንደንዴም የጎሳ መሪው በየሮቺ አማካኝነት በራዕይ እየተመሩ ሊመርጡ ይችላሉ[23]:: የጎሳ መሪው (Gabitatoo) አስተባባሪዎቹን ከመረጡ በኋላ ተጠሪነታቸውን ለራሳቸው አድርገው ያደራጃሉ:: እነዚህ አስተባባዎች፤ Qabechoo/ኢጋፋሪ-አማካሪ፣ Gepeindee/የጎሳ መሪ ባለቤት/፣ Koshenihoo/የፋይናንስ ሹም/ ፣ Koshetiguu /የግዥ ኃላፊ/ ናቸው:: እነዚህ የተለያየ የስራ ድርሻ ያላቸው አስተባባሪዎች በስራቸው ሌሎች አጋዥ ሰራተኞችን መርጠው በማደራጀት ኃላፊነታቸውን ይወጣሉ:: እነዚህ የኮሚቴ አባላት ለበዓሉ ብቻ የሚቋቋሙ ሳይሆን በጎሳ መሪው ተመርጠው የአካባቢውን ሰላም በማስፈን፣ የእርቅ ስርዓትን በማስፈጸም፤ የጉዶ ቅዱስ ስፍራዎችንና ደኖችን በመጠበቅና በማስጠበቅ እንዲሁም ሌሎች የባህል አስተዳደራዊ ስራዎችን ጭምር የሚሰሩ ናቸው:: የጎሳ መሪው የበዓሉን አስተባባሪዎች አደራጅተው ካጠናቀቁ በኋላ ለሁሉም የሸካቾ ጎሳ መሪዎች የበዓሉን ወርና ቀን በአማካሪዎቹ አማካኝነት ያስነግራሉ:: ምክንያቱም የጎሳ መሪዎቹ አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርጉ እና ከጎሳ መሪው ጎን ቆመው እንዲያግዟቸው እና የአጎራባች ጎሳ አባላትም ጉዶ ኬሶ ላይ ተገኝተው እንዲያከብሩ ለማሳወቅ ጭምር ነው::

---

[21] ቃ.መ አቴስታታ ዳኬቶ 11/08/14 ዓ.ም

[22] ቡ.ው አቴስታታ ዳኬቶ፣ ዘውዴ ግችላ፣ ዳምበራኖ አለሙ፣ ኦጎ ንገራሻ፣ ታምሩ ኮቶ፣ ወልታታ ባሀሩ፣ አምባሳደር አበራ በጭሮ፣ ወ/ሮ አሰገደች ሽታኖ ፣ንፈራሻ እሸቱ፣ፍቃዱ አውዶ፣ ቆመ ቆጭቶ 29/09/2014 ዓ.ም

[23] ቃ.መ አቴስታታ ዳኬቶ12/08/14 ዓ.ም

### 4.1.1. የመንጻት ሥርዓትን የመፈጸም ክዋኔ

የመንጻት ሥርዓትን ቀድሞ የመፈጸም ሥርዓተ ክዋኔ፤ በበዓሉ ላይ ሊሳተፉ ያሰቡም ሆነ የበዓሉን ስራ የሚከውኑ ሁሉም ከሚያረክሱ ነገሮች ተከልክለውና ነጽተው መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡ የመንጻት ህግን ቢተላለፉ እንኳን የመንጻት ሥርዓት ፈጽመው መዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ነጽቶ መቆየት በባህሉ፤ ከግብረስጋ ግንኙነት በመታቀብ እስከ በዓሉ ፍጻሜ ድረስ መዝለቅ መቻል ቀዳሚው ክልከላ ሲሆን ለምን ያህል ጊዜ የሚለው ደግሞ ቀኖናዊና በማህበረሰቡ ውስጥ ግለሰቦቹ እንዳላቸው ማህበራዊ ሚና እና ደረጃ የሚወሰን ነው፡፡ ይህም ጎሳ መሪው ጾም ከጀመሩበት ቀን አንስቶ እስከ አርባ ቀን ድረስ ራሳቸውን ከግብረስጋ ግንኙነት ሊያርቁ ይችላሉ፡፡ ከጎሳ መሪው ጋር በቅርበት የሚገናኙ ባለሟሎችም የጎሳ መሪውን ፈለግ ተከትላው ነጽተው መቆየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ነገር ግን በማህበረሰቡ ውስጥ እንደ ማህበራዊ ደረጃቸው ከአርባ ቀን እስከ ዘጠኝ ቀናት ድረስ ራሳቸውን ከግብረ ስጋ ግንኙነት ሊያቅቡ ይችላሉ፡፡ ወይም በዓሉ ላይ ለመሳተፍ ግብረስጋ ግንኙነት ሳይፈጽሙ ዘጠኝ ቀናት መቆየት በዓሉ እስኪጠናቀቅ ድረስም ከምንም ሳይነካኩ መዝለቅ ግድ ይላል፡፡ ለዘጠኝ ቀናት አስከሬን አለመንካት እና አስከሬን ከወጣበት ቤት አለመግባት፣ ለዘጠኝ ቀናት የሰው ደምም ሆነ የራስን ደም አለማፍሰስ፣ ኮሶ አለመታየት ወይም ከኮሶ ከሻሩ በኋላ ሰባት ቀን መቆየት፣ በወር አበባ ውስጥ አለመሆን፣ ከወር አበባ መንጻት በኋላ ዘጠኝ ቀናት መቆየት፣ ሰው አለመግደልን ያጠቃልላል፡፡

በተለይ ጎሳ መሪው፣ ቃበቾው (የጎሳ መሪው የቅርብ አማካሪ ወይም አጋፋሪ)፣ ገፐኢንዴ(የጎሳ መሪ የመጀመሪያ ባለቤት) እና ለበዓሉ የሚሆኑ ምግብና መጠጥ የሚያዘጋጁ አካላት ከየትኛህም የበዓሉ ተሳታፊዎች ቀድመው የመንጻት ስርዓትን መፈጸም ይጠበቅባቸዋል[24]፡፡

ጎሳ መሪው ከባለቤታቸው ተለይተው በአካባቢው የጉዶ ጎጆ (Keroo) ተሰርቶላቸው አርባ ቀን ጾም ጸሎት ይገባሉ፡፡ ፆሙ አንድም ከእንስሳት ተዋፅኦ ተለይቶ መቆየተን አንድም ደግሞ አቅም እስከተቻለ ሰዓት ድረስ ባዶ ሆድ መዝለቅን አንድም ደግሞ በጾም ወቅት ከግብረስጋ ግንኙነት መከልከልን ያጠቃልላል፡፡ የጎሳ መሪው የሚመገቧቸውን ምግቦች የመንጻት ሂደቷን የጨረሰች ባለቤቱ ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሰች እና የወር አበባ የማታይ ልጃገረድ ታሰናዳለች፡፡ ሴት ልጃገረዶች ባይኖሩ ደግሞ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወይም የመንጻት ሂደታቸውን የጨረሱ ወንዶች ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡  ምግቡ ከተዘጋጀ በኋላ ከጎሳ መሪው ጎጆ ራቅ ተደርጎ ይቀመጥላቸውና በቃበቾው አማካኝነት ለጎሳ መሪው እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ አርባ ቀን ሙሉ ጎሳ መሪው ባለቤታቸውን በአካል ጭምር ላያዩዋት ይችላሉ፡፡ ከጎሳ መሪው ጋር የሚገናኘው ቃበቾውም ጭምር እንደጎሳ መሪው ራሱን ከግብረስጋ ግንኙነት መጠበቅ፣ በንጽህና የተሰራውን ምግብ ብቻ መመገብ ይኖርበታል፡፡  የጎሳ

[24] ቃ.መ አምባሳደር አበራ በጭሮ 13/09/14 ዓ.ም

መሪው ባለቤቶች[25] በወር አበባ ሰዓት የጎሳ መሪ የሚጠቀምባቸውን ማንኛውንም ነገር መንካት አይችሉም፡፡ ቢነኩ እንኳ በጎሳ መሪው እና በራሳቸው ላይ መቅሰፍትን ያመጣሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ምናልባት የጎሳ መሪው ጾም በገቡባቸው ጊዜያቶች ባለቤቱ የወር አበባ ላይ ብትሆን ራሷን በተዘጋጀላት ጎጆ ውስጥ እስክትነጻ ታቆያለች፡፡

ነጽቶ የመጠበቅ ሥርዓተ ክዋኔ በዓሉ እስኪጠናቀቅ ድረስ መቆየት ግድ ይላል፡፡ በዓሉ ላይ መታደም የጀመረ ታዳሚም ሆነ ተሳታፊ ከጉዶ ኬሶ አካባቢ እንዲሄድ አይፈቀድለትም፡፡ ወደ ከተማ ቢሄድ እንኳን ወደ ከበራው ስፍራ እንዲመለስ አይፈቀድለትም፡፡ ምክንያቱም ብዙ ሊያረክሱ የሚችሉ ነገሮች ስላሉ ነው፡፡ ይህም የመንጻት ሥርዓት ያልፈጸመን ሰው ሊጨብጥ፣ እርሱ የተጠቀመበትን እቃ ራሱ ሊጠቀም ፤ አስከሬን የሄደበትን ስፍራ ሊረግጥ፣ ደም ሊነካ ወይም የመንጻትን ህግ ሳያውቀው ሊተላለፍ ይችላል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ በድፍረት ሄዶ እንኳን ቢመለስ መቅሰፍት ወደቤቱ ይገባል ተብሎ ይታመናል[26] በጉዶ የመንጻት ስርዓትን የፈጸመ የብሄረሰቡ አባልም ሆነ ከብሄረሰቡ አባላት ውጪ ያሉ ሰዎች መሳተፍ ይችላሉ፡፡ የበዓሉ ተሳታፊዎች ሁሉም ቢያንስ በዓሉ ላይ ከመታደማቸው አስቀድሞ ዘጠኝ ቀናት በፊት የመንጻት ስርዓትን ፈጽመው ማጠናቀቅ አለባቸው፡፡ የግብረስጋ ግንኙነት የፈጸመ፣ የወር አበባ ፈሳሽ ያለባት ሴት ወይም የቆሰለ እና ደም የሚወጣው ሰው በፍጹም ጉዶ አካባቢ መገኘት የለበትም፡፡ በድፍረት ተገኝቶ እንኳን ቢሆን ታላቅ ቁጣ ወደ ቤቱ ይገባል ተብሎ ይታመናል፡፡ እንዲህ አይነቱን ድፍረት የተላለፉ በርካታ ሰዎች በመቅሰፍት ተመትተዋል[27]፡፡ ነገር ግን በዘጠኝ ቀናት ውስጥ አስከሬን የነካ ቢኖር የመንጻት ስርዓትን የፈጸሙ የበዓሉ ታዳሚዎች ካሉበት በጣም ራቅ ብሎ ሥርዓቱን መከታተል ይችላል፡፡ ይሁንና የበዓሉን ተሳታፊዎችም ሆነ ታዳሚዎች እንዳያረክሳቸው መንካትም ሆነ መጨበጥ አይችልም፡፡ ጉዶ ሊከበር ዘጠኝ ቀናት ሲቀረው ጉዶ በሚከበርበት ቀበሌ ውስጥ ሰው ቢሞት በአካባቢው አይቀበርም፡፡ የአጎራባች ቀበሌ ነዋሪዎች አስከሬኑን ይዘው በመሄድ በአካባቢያቸው ይቀብሩታል፡፡ ይህ የሚሆነው አንድም መሬቱ እንዳይረክስ ሲሆን አንድም ደግሞ የጉዶ ተሳታፊዎችን እንዳያረክስ ነው[28]፡፡

ከመንጻት ሥርዓት ጋር ተያይዞ የዘጠኝ ቁጥር እሳቤ፤ የሸካቾ ብሔረሰብ የጎሳ መሪዎች የመንጻት ሥርዓቱን እንደ የመስዋዕት ክዋኔው ሁሉ በቀጥታ ከኦሪታዊው

[25] አንድ ጎሳ መሪ በባህሉ መሰረት አቅሙ እስከቻለ ድረስ እስከ ሶስት ሚስቶች እንዲያገባ ይፈቀድለታል፡፡ ዋና ምክንያቱም ጎሳ መሪው በጾም ጸሎት ወቅት አንድ ባለቤት ብቻ የሚኖራቸው ከሆነ ባለቤቱ በተፈጥሮም ሆነ በሌላ ምክንያት የመንጻት ህግን ልትተላለፍ ትችላለች፡፡ በዚህ ምክንያት የመንጻት ህግጋትን የሚጠይቁ የሀገረሰባዊ እምነቱ ክዋኔዎች በጠቅላላ እክል ይገጥማቸዋል፡፡ ከዚህ የተነሳ ነው ጎሳ መሪዎች ከአንድ በላይ ሚስት እንዲያገቡ የሚፈቀድላቸው ቃ.መ ዘውዴ ግችላ 17/09/14 ዓ.ም፡፡

[26] ቃ.መ ዘውዴ ግችላ፤13/09/14 ዓ.ም

[27] ቃ.መ ዳንበራዋ አለሙ፤17/09/14 ዓ.ም

[28] ቡ.ው አቴስታታ ዳኬቶ፣ ዘውዴ ግችላ፣ ዳምበራዋ አለሙ፣ ኦጎ ንገራሻ፣ ታምሩ ኮቶ፣ ወልታታ ባህሩ፣ አምባሳደር አበራ በጭሮ፣ ወ/ሮ አሰገደች ሽታዋ ፣ንፈራሻ እሸቱ፣ፍቃዱ አውዶ፣ ቆመ ቆጭቶ 29/09/2014ዓ.ም

የመንጻት ሥርዓት ጋር ያገናኙታል፡፡ "ማንኛውም ሰው በድንኳን ውስጥ ቢሞት ህጉ ይህ ነው፤ ወደ ድንኳኑም የሚገባ ሁሉ በድንኳንም ውስጥ ያለው ሁሉ ሰባት ቀን እርኩስ ይሆናል"(ዘሁልቁ 15፡19)፡፡ "ሴት ፈሳሽ ቢኖርባት በስጋዋም ያለው ፈሳሽ ነገር ደም ቢሆን፣ በመረገምዋ ሰባት ቀን ትቀመጣለች፤ የሚነካትም ሁሉ እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው" (ዘሌዋ. 15፡19)፡፡ ይህ ኦሪታዊው የመንጻት እሳቤ ከሸካቾ ብሔረሰብ የመንጻት ሥርዓት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም ከርኩሰት ለመንጻት በሚወስደው ጊዜ ግን የሁለት ቀናት ልዩነት አለው፡፡ ልዩነቱ የመጣው ብሔረሰቡ ለዘጠኝ ቁጥር ከሚሰጠው እሳቤ የተነሳ ነው፤ በብሔረሰቡ ዘጠኝ ቁጥር የንጽህና፣ የምልዑነት፣ የልዕልና ፣ የቅድስና፣ የጸሎት እና በፈጣሪ (በየሮቺ) ዘንድ የመሰማት ተምሳሌታዊ እሳቤ አለው[29]፡፡ የትኛውም ነገር በዘጠኝ ቀናት ውስጥ ፍጹም ንጹህ ይሆናል፤ ፍጹም ቅዱስ ይሆናል፤ ዘጠኝ ቀናትን በመንጻት ሥርዓት ውስጥ ያለፈ ሰው የየሮቺ ቁጣ ይደርስብኛል ብሎ አይፈራም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ማንኛውም ሰው እስከ ዘጠኝ ሰዓት ጾም ቢጾምና ዘጠኝ ሰዓት ላይ ተንበርክኮ ፈጣሪውን ቢለምን ጸሎቱ ያርጋል፤ ፈጣሪም ይሰማዋል[30]፡፡

በሸካቾ ብሔረሰብ በዘጠኝ ቀናት ውስጥ የመንጻት እሳቤ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ሲመረመር፤ "ከቀኑም ዘጠኝ ሰዓት ላይ ቆርኔሌዎስ ሆይ የሚለው የእግዚአብሄር መልዓክ ወደ እርሱ ሲገባ በራዕይ በግልጥ አየው፡፡ እርሱም ትኩር ብሎ ሲመለከተው ደንግጦ፤ ጌታ ሆይ ምንድር ነው? አለ፡፡ መልዓኩም አለው ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሄር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን አረገ" (ሐዋ.10፡3-4)፡፡ "ጴጥሮስና ዮሀንስም በጸሎት ጊዜ በዘጠኝ ሰዓት ወደ መቅደስ ይወጡ ነበር (ሐዋ. 3፡ 1)፡፡ "በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፡፡ አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ ማለት ነው (ማቴ. 27፡46)፡፡

ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች አንጻር፤ ከብሉይ ኪዳን መጻህፍ ውስጥ ከሸካቾ ብሔረሰብ የዘጠኝ ቁጥር እሳቤ ጋር የሚሰምር ጥቅስ አልተገኘም፡፡ ይሁንና የሸካቾ ብሔረሰብ ለዘጠኝ ቁጥር ያለውን ተምሳሌታዊ እሳቤ ከአዲስ ኪዳኑ እሳቤ ጋር ተመሳስሎ መገኘቱን ልብ ይሏል፡፡ በአዲስ ኪዳን ዘጠኝ ቁጥር ከሰዓት እሳቤ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ዘጠኝ ሰዓት እግዚአብሔር ጸሎትን የሚሰማበት፣ ጸሎት ወደላይ የሚያርግበት፣ እግዚአብሔር ወደ ሰዎች የሚያዘነብልበት እንደሆነ ከጥቅሶቹ መረዳት ይቻላል፡፡ የዚህ ጥናት መረጃ አቀባዮች የሰጡትን የዘጠኝ ቁጥር እሳቤ በመውሰድ ከመጽሃፍ ቅዱሱ እሳቤ ጋር ስናገናኘው በሀገረሰባዊ እምነቱ ላይ የአዲስ ኪዳን ወይም የክርስትና ተጽእኖ እንዳረፈበት መረዳት ይቻላል፡፡

---

[29] ቃ.መ. አምባሳደር አበራ በጭሮ 09/09/14 ዓ.ም

[30] ቡ.ው አቶ ዘውዴ ግችላ፣ አቴስታታ ዳኬቶ፣ ዳምበራኖ አለሙ ሸኖ፣ ኦጎ ንገራሻ፣ ወልታታ ባህሩ ገ/ጊዮርጊስ፣ አምባሳደር አበራ በጭሮ፣ ንፈራሻ እሸቱ፣ፍቃዱ አውዶ፣ ቆመ ቆጭቶ 29/09/2014ዓ.ም

### 4.1.2. ለጉዶ ኬሶ ክዋኔ የግብዓት አቅርቦት ዝግጅት

ለጉዶ ኬሶ ሥርዓተ ክዋኔ የግብዓት አቅርቦት ዝግጅት፤ ገፐኢንዴዋ(የጎሳ መሪው የመጀመሪያ ባለቤት) ከምትመራው የምግብና የመጠጥ ቅድመ ዝግጅት በተጨማሪ የአካባቢው ልጃገረዶች የመንጻት ስርዓትን መፈጸማቸውን እርግጠኛ ሲሆኑ በየቤታቸው የጤፍ ጠላ፣ ብርዝ ጠጅ፣ የእንሰት ውጤቶችን ያዘገጃሉ፤ በዓሉ ሲደርስም ጉዶ አካባቢ ወደ ተዘጋጀ ዳስ ሄደው ያስረክባሉ፡፡ በዓሉ አንድ ወር ሲቀረው ከመንጃ ጎሳዎች መካከል ጠንከር ያሉ ወንዶች ተመርጠው ጉዶ ያለበትን አካባቢ ያጸዳሉ፡፡ ለጽዳት እና ለምንጣሮ መንጃ ጎሳ የሚመረጠው አኗኗሩ ከተፈጥሮ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ስለሆነና ልባቸው የዋህ ስለሆነ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ መንጃዎች የመንጻት ስርዓት ፈጸሙም አልፈጸሙም ጉዶ አካባቢ ቢደርሱ መቅሰፍቱ አያገኛቸውም ተብሎም ይታመናል፡፡ ጉዶ አካባቢ ከጸዳ በኋላ በጎሳ መሪዎች ቁጥር የዳስ ጎጆዎች በአካባቢው ነዋሪዎች ይሰራሉ፡፡ ለበዓሉ የሚመጣው ግብዓት የሚሰበሰብበት የዳስ አደራሽም ይሰራል፡፡ ሁሉም የበዓሉ ተሳታፊዎች ያሏቸውን የክት የባህል ልብሶች አውጥተው ያጥባሉ ፤ ያሰናዳሉ፤ ቆሻሻ በማይነካው ስፍራም ያስቀምጣሉ፡፡ ወንዶች ለበዓሉ እንጨት በመፍለጥ ያዘጋጃሉ፡፡ በዓሉ ሲደርስም ለማብሰያ እንዲሆን ያዘጋጁትን እንጨት ሄደው ይሰጣሉ፡፡ እንጨት የሚፈለጠውም ከበዓሉ ቀን ዘጠኝ ቀናት በፊት ቀደም ተብሎ ነው፡፡ ምክንያቱም በፈለጣ ወቅት መድማት እንዳያጋጥም ነው፡፡ መድማት ካለ በዓሉ ላይ የመንጻት ህግን ተላልፏልና አይታደምም፡፡ ለመስዋዕት የሚሆነው ወይፈን ቀደም ተብሎ ይዘጋጃል፡፡ ይህ ወይፈን በግዥ፣ ወይም በስዕለት፣ ወይም ደግሞ ከጎሳ መሪው ግቢ ውስጥ ካሉት ሊመረጥ ይችላል፡፡ ምርጫው ወይፈን ከመሆኑ ውጪ ቀለማትን ያማከለ አይደለም፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለመስዋዕት መሰዊያ የሚሆን አዲስ ቢላ፤ ወይፈኑ የሚታሰርበት አዲስ ገመድ እና የባህል መሪው መስዋዕት ሊያቀርቡ ወደ ጉዶ ተራራ ሲገቡ ወገባቸው ላይ የሚታሰር ገመድ ይዘጋጃል፡፡ ለበዓሉ ታዳሚዎች የሚሆኑ በጎች፣ በሬዎች እና ላሞች በግዥ ወይም በስዕለት መልክ ይቀርባሉ፡፡

## 4.2. የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ በዕለተ ቀኑ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ በዕለተ ቀኑ ከበራው ከጀመረበት አንስቶ እስከ ማብቂያው ድረስ ያለው የክዋኔ ሂደት ይቀርባል፡፡

### 4.2.1. የዳግም መንጻት ክዋኔ

የዳግም መንጻት ሥርዓተ ክዋኔ፤ የጉዶ ኬሶ ሥርዓተ ከበራ ከመጀመሩ ጠዋት ከ አንድ ሰዓት ቀደም ብለው የአቴሶ ጎሳ መሪ አቴስታታ ዳኬቶ እና የአዶ ጎሳ መሪ ጎግራሻ መጅቶ አቅራቢያቸው ወዳለ ወንዝ በመሄድ የመንጻት ሥርዓትን ይፈጽማሉ። የመንጻት ስርዓትን ለመፈጸም የደዶ (Deddo) እንጨት ከነቅጠሉ ዳርና ዳር ይቆማል፤ የእሳት እራት ከነህይወቷ ተይዛ ከቆመው እንጨት ላይ ክንፏ ንጫቶ/Nichatto/ በሚባል ቀጭንና ጠንካራ ሀረግ ይታሰራል፡፡ በመቀጠል ሁለቱ የአቴሶ እና የአዶ ጎሳ መሪዎች አንድ ላይ እጅ ለእጅ በመያያዝ ፍየል አርደው የቆመው እንጨት ርብራብ ላይ በማኖር ያቃጥሉታል፡፡

ፍየል ለመስዋዕት ማቅረባቸውና ደም ማፍሰሳቸው በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የተሰራ ሃጢኣትን ለማስተስረይና ለመንጻት ነው። ፍየል ሲያርዱ ሁለቱ ጎሳ መሪዎች እጅ ለእጅ መያያዛቸው፤ እኛ ነጽተናል፤ ለመስዋዕቱም ተባብረናል፤ ሥርዓቱን ለማስቀጠል ተማምለናል የሚለውን ሲያጠይቅ ነው[31]። እሳት እራት በቀጭን የሀረግ ሳር መታሰሯም የመንጻት ሂደትን ካስተጓጎለ ነገር ሙሉ ለሙሉ መንጻትን ማረጋገጫ ነው። ምክንያቱም እሳት እራት በሸካቾ ባህል የብርሃን የመልካም ነገርና የንጽህና ተምሳሌት ስለሆነች ነው። እሳት እራት ብርሃን በሌለበት አትበርም፤ ጨለማን ትፈራለች፤ ህብረቷ ከብርሃን እንጂ ከጨለማ አይደለም ሲል ነው፤ እሳት እራቷ በቀጭን ሀረግ መታሰሯ በወንድም ጎሳዎች መካከል ያለውን የማይነጣጠል ህብረት ሲያመለክት ነው[32]።

የመንጻት ስርዓት ከፈጸሙ በኋላ ሁለቱ የጎሳ መሪዎች ወደ ጉዶ ኬሶ ቅዱስ ተራራ ከሁሉ ቀድመው ያቀናሉ[33]። የከበራው ታዳሚ እስኪሰባሰብ በጽሞናና በጸሎት ለተወሰኑ ደቂቃዎች ይቆያሉ። ከጠዋቱ አምስት ሰዓት ገደማ የበዓሉ ታዳሚዎች እና ተሳታፊዎች ወደ ጉዶ ስፍራ እየተመሙ ይደርሳሉ።

### 4.2.2. የሚታዊ ( Myth) ተረክ ክዋኔ

የሚታዊ ተረክ ሥርዓተ ክዋኔ፤ ልክ ከረፋዱ አምስት ሰዓት ሲል የጎሳ መሪው አማካሪ(ቃበቾ) ከተቀመጠበት ተነስቶ ስለ ጉዶ ኬሶ የመስዋዕት ሥርዓተ ክዋኔ አፈጻጸም እንዲናገሩ ጎሳ መሪውን ይጋብዛል። የጎሳ መሪው ከተሳታፊዎቹ ፊት ለፊት ቆመው ከፍ ባለ ድምጽ፤ "እንኳን ደህና መጣችሁ፤ በዓሉን በሰላም የሚያስጀምረን የሮቺ እንዲሁ በሰላም ያስጨርሰን" ሲሉ፤ ታዳሚው ከፍ ባለ ድምጽ "አሜን" በማለት ምላሽ ይሰጣል። ቀጥለውም፤ "ይህን የመባ በዓል የምናዘጋጅለት የሮቺ ብቻ ሳይሆን እርሱ የሚያርፍበት ይሄ ተራራ ህይወት እንዳለው ታውቃላችሁ?" ብለው ይጠይቃሉ። ታዳሚው "አዎ" ይላል። በመቀጠል ተከታታይነት ያላቸውን ተረኮች ለታዳሚው ማቅረብ ይጀምራሉ።

> ጉዶ ህይወት አለው። ሁላችሁም ሰምታችኋል። ከዚህ ቀደም የጉዶን ቅዱስ ስፍራ አርክሰን፣ ደን ውስጥ ገብተን፣ የማይቆረጠውን ቆርጠን፣ ጉዶ ተቆጥቶን ታላቁ አለት እንደ ጎማ ተንከባሎ ሄዶ ነበር። የሄደው የበደላችን

---

[31] ቃ.መ ጎግራሻ መጅቶ 19/09/2014 ዓ.ም

[32] ቡ.ው አቴስታታ ዳኬቶ፣ ዘውዴ ግችላ፣ ዳምበራኖ አለሙ፣ ኦጎ ንገራሻ፣ ታምሩ ኮቶ፣ ወልታታ ባህሩ፣ አምባሳደር አበራ በጭሮ፣ ወ/ሮ አሰገደች ሽታኖ ፣ንፈራሻ እሸቱ፣ፍቃዱ አውዶ፣ ቆመ ቆጭቶ 29/09/2014ዓ.ም

[33] ከ1966 ዓ.ም በፊት የፍየል እርዱ ከተከናወነ እና ሁለቱ የጎሳ መሪዎች የመንጻትን ስርዓት ከፈጸሙ በኋላ ወንዙን ተሻግረው ወደ ታላቁ ጎሳ ድንበር በመሄድ የሁለት ወንድማማች እናት የተቀበረችበት ቦታ ላይ በሬ ይታረድ ነበር፡፡ ምሳሌ አበሎ እና አቴሶ ፣ጫጎ ና የፖ ጎሳዎች የአንድ እናት ልጆች ናቸው፡፡ ከዛም ስጋውን እኩል ይካፈላሉ ፡፡ ቆዳው ተቆራርጦ ለሁሉ ሰው እኩል ይሰጣል፡፡ ይህ ምርቃት ነው፡፡ እድሜ ልክ ለልጅ ልጅ ይተላለፋል፡፡ ይህ የቆዳ ቁርጥራጭ ሹግዮ/Suguuye/ ይባላል፡፡ ይህ አንድነትን ፍቅርን መያያዝን ያመለክታል፡፡ ወደ አንድ ጥላ መሰባሰብን ያመለታል፡፡ ይህ ክዋኔ እስከ 5 ሰዓት ድረስ ቆይቶ ነው ወደ ዋናው ጉዶ የሚኬደው፡፡ አሁን አሁን ግን ይህ ክዋኔ ካለው የኢኮኖሚ አቅም የተነሳ እየቀረ መጥቷል፡፡ (ቃ.መ ኦጎ ንገራሻ 16/09/14 ዓ.ም)

> ጽዋ ሞልቶ ነው፡፡ አላከበርነውም፤ ሽማግሌዎችን ማክበር፤ የጎሳ መሪዎችን ሀሳብ መቀበል አቅቶን ሄዶ ነበር፡፡ ይህንን በተጨባጭ ካዩት አያቶቻችሁ ሰምታችኋል፡፡ ጉዶ ህይወት አለው፡፡ ጉዶ ውስጥ የቤት እንስሳቶች እየወጡ ይገባሉ፡፡ ታውቃላችሁ ጉዶ ሰው መስሎ ከተራራው ይወጣና በጉዶ አካባቢ ሳይፈቀድላቸው የሚሄዱ ሰዎችን ከተመለከተ ይሞታሉ፡፡ በዚህም በርካታ ወገኖቻችንን አጥተናል፡፡ የምናከብረው፤ መስዋዕት የምንሰዋለት ይህንን ለመከላከል እና ስለሰጠን ሰላም ፣ ስላበዛልን በረከት ስንል ነው፡፡ ጉዶ ጥሎን ሲሄድ ሰላማችን ደፈረሰ፣ ጤናችን ታወከ፣ ሰማይ መሬቱ ተጣሉ[34]፤ ምርት ረድኤቱ ጠፋ፡፡ አሁን ግን የሮቺ ይመስገን ጉዶ ተመልሶልናል፡፡

ብለው ሲጨርሱ ሴቶች በእልልታ ወንዶች በጭብጨባ የጎሳ መሪውን ንግግር ሲቀበሉ መመልከት ተችሏል፡፡ ጎሳ መሪው አቴስታታ ዳኬቶ ስለ ጉዶ መተረካቸውን ይቀጥላሉ፤

> ከዛሬ መቶ አመት በፊት የሆነውን ሰምታችኋል፤ አንድ ኃይለኛ ነብር ጉዶ ውስጥ ገብቶ ከጉዶ እየወጣ በርካታ የሰው ከብት ጨረሰ፡፡ እናም አንዱ የኛ ጎሳ አባል 'በገመድ እሰሩኝና ልግባ፤ የሰው ከብት ከሚያልቅ' አለ፡፡ አያቶቻችን በሁለት ረጃጅም ገመድ ወገቡን አስረው አስገቡት፡፡ ወደ ጉዶ እየቀረበ ሄደ፡፡ ልክ ጉዶ ጋር ሲደርስ፤ ልጃገረድ የምትመስል ሴት ቆማ ተመለከተ፤ ከእርሷም አጠገብ ያ የሰዉን ከብት እየበላ ያስቸገረውን ነብር ተመለከተ፡፡ ልጃገረዷም መፍራቱን ተመልክተታ 'አትፍራ! አይዞህ! በዚህ የብረት ዘነዘና ግደለው! ና ውሰድ!' አለችው፡፡ 'ከገደልከው በኋላ ምስክር ይሆን ዘንድ ዘነዘናዋን ቤት ወስደህ አስቀምጥ' አለችው፡፡ ሰውየው ነብሩን ገደለና እየጎተተ ከጉዶ ውስጥ አወጣው፤ ዘነዘናዋንም ወስዶ ጎጆ ቀልሶ ለብቻ አስቀምጧታል፡፡ እስከዛሬ ድረስ ይህች ብረት ከልጅ ልጅ እየተላለፈች ቂጦ ጌሻ ከፋ ውስጥ ትገኛለች፡፡

ብለው ሲጨርሱ፤ ታዳሚው "አዎ" አለ፡፡ ጎሳ መሪው አቴስታታ ዳኬቶም ይቀጥላሉ፤

> አሁን በእኔ ዘመን ከዛሬ ሃምሳ አመት በፊት በእኛ አቴሶ ቀበሌ ውስጥ ከፊት ለፊታችን ካለው ጋኮቺ ጉዶ አካባቢ ብዙ ሰዎች ጉዶን ንቀው ጎጆ ቀልሰው ጉዶ አካባቢ መኖር ጀምረው ነበር፡፡ ሰውም እየበዛ እና እየረበሸ አስቸገረ፡፡ ከዛም አንድ ቀን በጣም ቆንጆ ልጃገረድ ሹሩባ ተሰርታ በአካባቢው ወዲህ ወዲያ ስትል ሰዎች ተመለከቱ፡፡ የተመለከቷት ሰዎች 'የማነሽ ቆንጆ ነይ ነይ…' እያሉ ተከትለዋት እስከመጨረሻ ሲሄዱ ጉዶ አካባቢ ደረሱ፡፡ የጉዶ በር ተከፈተና ልጃገረዷ ወደ ውስጥ ሰተት ብላ ገባች፡፡ በዛን እለት የተመለከቷት ከ ሶስት መቶ በላይ የሚልቁ ሰዎች በሳምንት ጊዜ ውስጥ ህይወታቸው አለፈ፡፡

---

34 ዝናብ መጥፋት፣ ድርቅ መሆን

ብለው ሰጨርሱ የተሰበሰቡት ታዳሚዎች አብዛኞቹ ፊታቸው በሃዘን ሲደበዝዝ፤ የቅርብ ጊዜ ትውስታ በመሆኑ ይመስላል ፊታቸው ሲጨፈግግ፤ አይናቸው በእንባ ሲሞላ በተደረገው ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ጎሳ መሪው፤ ሁሉንም ታዳሚዎች እየተመለከቱ፤

> በ2007 ዓ.ም ኤሚሊ ዊልያም  የምትባል አንድ እንግሊዛዊ ወደ እኛ ጥናት ለማድረግ መጥታ ነበር፡፡ አካባቢውን ማጥናት ፈልጋ እኔ ጋር ተገናኝታ ነበር፡፡ ከሌሎች የጎሳ መሪዎች ጋር ተነጋግረን እንደማይቻል፣ ጉዶ ሊቆጣን እንደሚችል ነገርናት፡፡ ይሁንና መቼም ለመልካም ነው ጥናቱ ከተጠና አካባቢያችንንም ይጠቅማል ብለን ፀሎትና ልመና አድርገን ወደ አካባቢው አቀናን፡፡ ወደ ጉዶ አለት ልንደርስ በግምት አንድ ኪሎ ሜትር ሲቀረን ማጉያ መነጽሯን አንስታ ወደ ጋኮቼ ጉዶ ተመለከተች፡፡ ቀስ እያለች እያቀረበች ስትመለት ጉዶ ላይ አንድ ነገር ተቀምጦ በማየቷ በጣም ደነገጠች! ለመሮጥም ሞከረች፡፡ መነጽሩን ለእኔም ሰጠችኝ ተመለከትኩ፡፡ ያየሁት ነገር ለራሴም አስደነገጠኝ፤ አካሉ ከዝሆን ጋር እኩል ይሆናል፤ ጸጉር የለውም፤ ጆሮው እንደዝሆን ጆሮ ትልቅ ነው፡፡ ለእኛ ጀርባውን ሰጥቶ ሰውነቱን ግራና ቀኝ እያንቀሳቀሰ ቁጭ ብሏል፡፡ ለዳንበራኖ አለሙ አሳየሁት እሱም ያየውን ማመን አቃተው፡፡ ኤሚሊ ዊልያም በአስተርጋሚዋ በኩል እንዲህ አለችን 'ጉዶ ህይወት አለው፤ ይህ አይነቱ ክስተት  አካባቢው ላይ ለዓለም የሚተርፉ በርካታ ማዕድናት መኖራቸውን ያሳያሉ፤ አከባቢው ላይ ተጠግተው የሚኖሩ ሰዎችም በፍጥነት ስፍራውን ይልቀቁ፤ ምክንያቱም ይህ ልዕለተፈጥሯዊ[35] አካል በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ ሰዎችን ከተመለከተ ሰው ሁሉ ያልቃል ፤ ብላ አካባቢውን ጥላ ጥናቷን ሳታጠናቅቅ ለቃ ወጣች፡፡

በማለት አቴስታታ ዳኬቶ ተረኮቹን ጨርሰው ሲቀመጡ ታዳሚው በእልልታ እና በጭብጨባ ያጅቧቸዋል፡፡ ሁሉም እንደ አቅሙ፤ እንደችሎታው በለሆሳስ "ፈጣሪ እድሜዎን ያርዝመው፤ ክፉ አይንካዎ፤ ዘርዎ ገኝ ሆኖ ይቀጥል… "እያለ ዝግ እና ከፍ ባለ ድምጽ ሲመርቃቸው መመልከት ተችሏል፡፡

ከጎሳ መሪው ተረክ በመነሳት ጉዶ ራሱን በብዙ መንገዶች እንደገለጸ መረዳት ይቻላል፤ ጉዶ ራሱን በነገሮች የገለጸበት ምክንያት ለአማኙ ቅርብ መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ በሴት ልጅ ተመስሎ ከሁሉ አንሶ የተገለጠውም የሰውን የሴሰኝነት ባህሪ ለማሳየትና  መቅሰፍት ለማውረድ ነው፡፡ እየተንከባለለ በሚሸሽ ጎማ ተመስሎ ራሱን የገለጸውም ፊቱን ከአማኙ ላይ ዞር ማድረጉን ለመግለጥ ነው፡፡ ዝሆን መስሎ በመታየት የተገለጸውም የታላቅነቱን ኃይል፣ የክብሩንና የባለጸግነቱን መጠን ለመግለጽ ነው[36]፡፡

---

[35] አጽንኦቱ የራሴ ነው፡፡

[36] ቡ.ው፤ አቴስታታ ዳኬቶ፣ ኦጎ ንፈራሻ፣ ዳምቤራኖ አለሙ 29/09/14 ዓ.ም) አጽንኦቱ የራሴ ነው፡፡

የሮቺ በጉዶ ላይ አድሮ አማኙን ይመለከታል፣ ይሰማል፣ በንጽህና እና በቅድስና የሚቀርበውን መስዋዕት ተመልክቶ ይቀበላል፣ እንባን ያብሳል፣ ሰማይ ምድሩን ይታረቃል፣ በተቀደሰው የጉዶ ደን የሚደርሱትን፣ ዕጽዋት የሚቆርጡትን፣፣ ቅዱሱን ደን የሚያረክሱትን፣ በደል የሚፈጽሙትን ይቀጣል፣ መቅሰፍትን ወደ ቤታቸው ይልካል፣ ፊቱንም ያዞራል ተብሎ በሸካቾ ብሔረሰብ ይታመናል[37]፡፡

ከተወሰነ ደቂቃ እረፍት በኋላ የጎሳ መሪው አማካሪ ቃበቾው ከተቀመጠበት ተነሳና ቀጥሎ ያለውን መርሃ ግብር ያስተዋውቃል፣ "ቀጣዩ መረሃ ግብር ታዳሚዎች በዝምታ ጸሎት ውስጥ ሆነው ጎሳ መሪው ለጉዶ የሚቀርበውን መስዋዕት የሚያቀረቡበት ስለሆነ ሁላችሁም በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በልባችሁ የሮቺን እየለመናችሁ ተጠባበቁ" ይላል፡፡ ታዳሚውም የቃበቾውን ምክር ሰምቶ በዝምታና በእርጋታ ይዋጣል፡፡

### 4.2.3. መስዋዕት የማቅረብ ክዋኔ

መስዋዕት የማቅረብ ሥርዓተ ክዋኔ፣ ልክ ከቀኑ ስድስት ሰዓት ላይ የአቴሶ ጎሳ መሪ አቴስታታ ዳኬቶ ተነስተው ይቆማሉ፡፡ ጥቁር ልብስ (ማቅ) ይዘጋጅላቸዋል፡፡ ለጸጉራቸው መሸፈኛ ከጥቁር የወይፈን ቆዳ የተሰራ ኮፍያ፣ ከወገባቸው በላይም እንዲሁ ከጥቁር የወይፈን ቆዳ የተሰራ ልብስ(ካባ) ይለብሳሉ፡፡ ጥቁር የመልበሳቸው ትዕምርት የበደል እና የኃጢያት ምሳሌ መሆኑን ሲያመለክት ነው፡፡ እኔም ሆንኩ ህዝቡ ሳናውቅ በስህተት አውቀንም በድፍረት የሰራነውን ኃጢያት ከፊትህ ለብሼ መጥቻለሁና ይቅር በለን የሚል አንድምታ አለው[38]፡፡ የጎሳ መሪው አገልጋዮች ለመስዋዕት የሚሆነውን ወይፈን፣ ቢላ ዋንጫ፣ ገመድና የደም መርጫውን ይዘው ከጎሳ መሪው ፊት ይቆማሉ፡፡ ጎሳ መሪውም አጠገባቸው ወደ ቀረበው መስዋዕት እየተመለከቱ "እኔ ንጹህ ነኝ ባህል የከለከለውን ሁሉ አክብሬያለሁ፡፡ የመንጻት ስርዓትን ፈጽሜያለሁ፣ እናንተም ይህንን ስርዓት ፈጽማችኋል፣ የመንጻት ስርዓቱን ያልፈጸማችሁ እኔ ከዚህ በደል ሁሉ ንጹህ ነኝ፡፡" በማለት ከፍ ባለ ድምጽ ለተሳታፊዎቹ ይናገራሉ፡፡ የበዓሉ ተሳታፊዎች በዚህ ሰዓት "አዲ አቤ… አዲ አቤ…9X" በማለት በጉልበት ተንበርክከውና መሬቱን እየሳሙ ለየሮቺ መጮህ ይጀምራሉ፡፡ ከታዳሚዎቹ መካከል በእድሜ አንጋፋ የሆነው አዲ…..አቤ ብሎ ያስጀምራል፣ ታደሚውም እሱን እየተከተለ ዘጠኝ ዘጠኝ ጊዜ አዲ አቤ በማለት ይከተላል፡፡ ትርጉሙ፣ 'አቤቱ ፈጣሪ ሆይ ተለመነን' ማለት ነው፡፡ ዘጠኝ ጊዜ አዴ አቤ ማለታቸው፣ ጸሎታቸው የመሰማቱ ማረጋገጫ በመሆኑ ነው፡፡ ከተማጽኖ ልመናው ቀጥሎ ለጎሳ መሪው አንጋፋ የሆነው የሌላ ጎሳ መሪ ጸሎት ማድረግ ይጀምራሉ፡፡ ጸሎቱ፣

> የሮቺ ሆይ ጎሳ መሪውን እርዳቸው፣ ወዳንተ መስዋዕት ሲያቀርቡ ይመጣሉና፣ ከሚዋጋ እሾህ አንተ ጠብቃቸው፣ እንቅፋት እንዳይመታቸው

---

[37] ቃ.መ. ዳንበራኖ አለሙ 09/09/14 ዓ.ም

[38] ቃ.መ. አምባሳደር አበራ በጭሮ 12/09/14 ዓ.ም

> ከልክልላቸው፡፡ተናዳፊና ተናካሽ ነገር እንዳይጎዳቸው አንተ ጠብቃቸው፡፡ ምናልባት በደል ቢኖርባቸው ይቅር በላቸው፤ ወደ ጉዶ በሰላም ገብተው በህይወት ይመለሱ፤

የአንጋፋው ጎሳ መሪ ፀሎት ትኩረት ያደረገው ጎሳ መሪው መስዋዕት ሊያቀርቡ ወደ ጉዶ ውስጥ ሲገቡ አደጋ እንዳይገጥማቸው የሚማጸን ነው፡፡ ፀሎቱ ሰውነታቸው ላይ ከሚደርስ አነስተኛ አደጋ  እስከ  የህይወት መስዋእትነት ድረስ ሊያደርስ የሚችል አደጋ አለና የሮቼ ከዚህ አደጋ እንዲጠብቃቸው የተደረገ የተማጽኖ ጸሎት ነው፡፡ በጎሳ መሪው ላይ ሊደርስ የሚችል የትኛውም የአካል ጉዳት በሚቀርበው መስዋዕት ላይ ታላቅ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ ጎሳ መሪው ድንገት ሰውነታቸው በእንቅፋት ወይም በእሾህ ቢደማ የመንጻቱን ሂደት አደናቅፏልና የሚቀርበው የደምና የሚቃጠል መስዋት ተቀባይነት አይኖረውም፤ ይህ ሁነት አንድም የሰው ደም በተቀደሰ ስፍራ ላይ ፈሷልና ስፍራው ይረክሳል፤ በመርከሱም ከበራው ይቋረጣል፡፡ ምናልባት ደግሞ በጎሳ መሪው በደል ምክንያት መስዋዕት ሊያቀርቡ ወደ ጉዶ ቅዱስ ስፍራ ሲገቡ ህይወታቸው ቢያልፍ እንኳን የጉዶ ሥርዓቱ ሙሉ በሙሉ ከመከወን ይቋረጣል፡፡ ምክንያቱም አንድም ስፍራው ላይ ህይወት ስለጠፋ ስፍራው እስኪነጻ ድረስ የረከሰ ስለሆነ ነው፤ አንድም ደግሞ ታዳሚው ሬሳ ያለበት ስፍራ ላይ ተገኝቷልና የመንጻት ቀኖናዊ ሥርዓትን አውቆም ይሁን ሳያውቀው ተላልፏል፡፡ በዚህ ምክንያት የጉዶ ከበራው ይቋረጥና ከ ዘጠኝ ቀናት የመንጻት ስርዓት በኋላ ዳግም የጉዶ ክዋኔው እንዲጥል ይደረጋል[39]፡፡ በመቀጠል ለመስዋእት የተዘጋጀውን ወይፈን ቃበቾው እና የመንጻት ሥርዓትን የፈጸሙ አገልጋዮች ወይፈኑን፣ የመስዋእት ቢላውን እና የወገብ ማሰሪያ ገመዱን ይዘው ከጎሳ መሪው ጋር ወደ ተራራው ይወጣሉ፡፡ የጎሳ መሪው እርዱን ከመፈጸማቸው በፊት፤ የሚከተለውን ጸሎት ያደርጋሉ፡፡

> የሮቼ ሆይ ይህንን መስዋዕት በአንተ ስም እሰዋለሁ፤ አንተ ይህንን መስዋዕት ተቀበል፤ ስለሰጠኸን ሰላም ፤ ስለሰጠኸን ጤና እና በረከት ሁሉ ይህንን መስዋእት አቀርባለሁ፤ በቀጣይም ለምድራችን ሰላምን፣ ለህዝባችን ጤና እና በረከትን አብዛልን፤ የሰራነውን በደል ሁሉ ይቅር በለን፡፡

በማለት ወይፈኑን በቀኝ በኩል አስተኝተው ሊባርኩት ሲዘጋጁ ወይፈኑ በጎርናና ድምጽ መጮህ[40] ይጀምራል፤ ሳለመታረድ በጣም ይንፈራገጣል፤ የወይፈኑ መጮህና

[39] ቡ.ው፤ አቴስታታ ዳኬቶ፣ ኦጎ ንፈራሻ፣ ዳምቤራኖ አለሙ 29/09/14 ዓ.ም) አጽንኦቱ የራሴ ነው፡፡

[40] ወይፈኑ ሊታረድ ቀንዱ ተይዞ እግሩ ታስሮ ጎሳ መሪው ከወይፈኑ ፊት ለፊት ቆመው ከመባረካቸው በፊት ወይፈኑ ካልተንፈራገጠ እና ጎርናና ድምጽ ካላወጣ፣ አንድም ጎሳ መሪው አንድም አገልጋዮቹ አንድም ደግሞ ከተሳታፊዎቹ መካከል የመንጻት ሂደትን ያልፈጸመ ሰው አለና መስዋእቱ ሳይቀርብ ይቆማል፡፡ ወይፈኑ ጮሆ ከሆነ ግን መስዋዕት የማቅረቡ ሂደት ይቀጥላል፡፡ ወይፈኑ እንዳለመታደል ሆኑ ባይጮህ የጎሳ መሪውና  የመንጻት ስርዓትን ፈጽምናል ያሉ የጎሳ መሪዎች ወደ መስዋእት ማቅረቢያው ቀረብ ብለው "አዴ አቤ" አቤቱ ይቅር በለን፣ በማለት ጸሎት ያደርጋሉ፡፡ ከደቂቃዎች በኋላ ለአንደኛው የጎሳ መሪ የሮቼ በድምጽ ወይም ደግም በራዕይ ይነግረዋል፡፡ ከየሮቼ በተረዳው መሰረት ጥፋተኛውን ይለያል፡፡ ተለይቶም ከጉዶ አካባቢ እንዲሄድ ይደረግና በምትኩ ሌላ ሰው ይቀየራል፡፡ በዛ ሰው ላይ ግን መቅሰፍት ይገባል፣ በበሽታ ይሰቃያል፣ በሂደትም ይሞታል(ቃ.መ ንፈራሻ እፊቱ)፡፡

መንፈራገጥ የሮቺ መስዋዕቱን ለመቀበሉ ታላቅ ማረጋገጫ ነውና[41] የወይፈኑን ሁኔታ ሲጠባበቅ የነበረው ታዳሚ ከተቀመጠበት ተነስቶ በእልልታ እና በጭብጨባ አካባቢውን ፤ በጡሩንባ እና በከበሮ ክዋኔውን ያደምቀዋል፡፡

በመቀጠል ጎሳ መሪው ወይፈኑን እየሰዉ ባለበት ወቅት ቃበቾው(የጎሳ መሪው አማካሪ-አጋፋሪ) ደሙን በዋንጫ ቀድቶ ለጎሳ መሪው ይሰጣቸዋል፡፡ ከዛም በአገልጋዮቹ አማካኝነት የጎሳ መሪው ወገብ ላይ ገመድ ታስሮ ጉዶ ወዳለበት ተራራማ አለት ደሙን በዋንጫ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ ጉዶ ጋር ሲደርሱ ደሙን አለቱ ላይ በመርጫ ይረጩታል፡፡

በጎሳ መሪው ወገብ ላይ ገመድ የመታሰሩ ሚስጢር ጎሳ መሪው በኃጢያት መተላለፍ ምክንያት እንኳን ህይወታቸው ቢያልፍ አስከሬናቸውን ጎትቶ ከዋሻው ውስጥ ለማውጣት ታስቦ ነው፡፡ ነገር ግን  በዕለቱ ጎሳ መሪው ምንም ሳይሆኑ ደሙን አለቱ ላይ ረጭተው ወደ ተሰዋው ወይፈን ተመልሰዋል፡፡



ፎቶ 1፤ ጎሳ መሪው ለጉዶ መስዋዕት አቅርበው ወደ ተሳታፊው ሲመለሱ (በጥናት አቅራቢው)

ጎሳ መሪው ወይፈኑ ወደ ተሰዋበት ስፍራ ሲደርሱ አገልጋዮቹ በጣም የደረቀ አራት የዶቅማ እንጨት ወስደው በአራት ማዕዘን መሬት ላይ ይተክላሉ፡፡ ሌሎች በርከት ያሉ ከደረቅ የዶቅማ እንጨቶች የተዘጋጁ ርብራቦችም አራቱ እንጨቶች ላይ ይረበረባሉ፤ ርብራቡ ላይ የመስዋዕቱን ወይፈን ጎሳ መሪውና አገልጋዮቹ አንድም ሳይቀር እየቆራረጡ ወደ ርብራቡ ይጥሉታል፡፡ በመቀጠል የጎሳ መሪው ቃበቾ(አጋፋሪ) ምንም ነገር ያልነካውና ያልረከሰ ሁለት የዶቅማ እንጨቶችን በማምጣት አፋጭቶ እሳት ያወጣል፡፡ እሳቱ ከተቀጣጠለለት በኋላ  ወደ ሚቃጠለው መስዋዕት እሳቱን ይዞ ይሄዳል፡፡ ጎሳ መሪውና አገልጋዮቹ ተረባርበው መስዋዕቱን ያቃጥሉታል፡፡ መስዋዕቱ እየተቃጠለ ባለበት ወቅት ለዚሁ ዓላማ ብቻ የተዘጋጀ

[41] ቃ.መ ወልታታ ባሀሩ ወ/ጊዮርጊስ 08/09/14 ዓ.ም

በርበሬና ልዩ ልዩ ቅመማ ቅመሞች መስዋእቱ ላይ በመጨመር አብሮ እንዲቃጠል ይደረጋል፡፡ ይህ የሚሆነው የሮቺ የመስዋዕቱን መዓዛ ይበልጥ እንዲያሸት ነው፡፡ የሚቃጠለው መስዋዕት እየተቃጠለ ባለበት ወቅት ታዳሚው ምስራቸ(እንኳን ደስ አለን) የሚለውን የደስታ ዘፈን ይዘፍናል፡

| | |
|---|---|
| *Mshirachaa/2x/* | *የምስራች… የምስራች /ከዋኝ/* |
| *Oho…Mshirachaa* | *ኦሆ……የምስራች/ተሳታፊ/* |
| *Yero Nodejon nogana daee* | *የሮቺ መስዋዕታችንን ተቀበለን* |
| *Nowo ogiq ermione* | *እኛም በደንብ ተደሰትን* |
| *Nogonde buloon Noss qayee* | *የሮቺ ሁሉን ይቅር አለን* |
| *Bikaron nogane biokstos* | *የሮቺ ቁጣውን አራቀልን* |
| *No galatewone* | *እኛም አመሰገንነው* |
| *Shamawoso dig tunayee* | *በሰማይ ሰላም ሆነ* |
| *Shawoso dig tunayee* | *በምድር ሰላም ሆነ* |
| *Nokacoo nos wotaye* | *ምርኳችን ተመለሰ* |
| *Bulii digo nos tunayee* | *ሰላም ጤናችን ተመለሰ* |
| *Nokaro shuno Metye* | *ቤታችን ፍቅር ሆነ* |
| *Gane dono diryaye* | *ሴት ወንዱ ተባረከ* |
| *No ermiwone* | *እኛም ተደሰትን* |
| *Oho…Mshirachaa/9 X/* | *ኦሆ……የምስራች/9X/ (ትርጉም)*[42] |

የምስራቻ ዘፈን ከመጀመሩ በፊት በግራና በቀኝ ከዋኝና ተሳታፊ አንድ ላይ በሁለት ረድፍ ፊት ለፊት እንዲተያዩ ሆነው ይቆማሉ፡፡ አንዳንዶቹ በእጃቸው ጋኛና ጦር ይይዛሉ፡፡ ጎሳ መሪው ትንሽ ፈቀቅ ብለው ቆመዋል፡፡ የጎሳ መሪው አገልጋዮች መለከትና ከበሮ በመያዝ ግራና ቀኝ ለጭፈራ ከቆሙት ተሳታፊዎች ትንኝ ዝቅ ብለው መለከቱን ለመንፋትና ከበሮውን ለመምታት ተዘጋጅተዋል፡፡ ተሰታፊ መስለው ከቆሙት መካከል አንዱ ከዋኝ "ምስራቻ… ምስራቻ" ብሎ ከፍ ባለ ድምጽ በዜማ ሲጀምር ተሳታፊዎቹ ደግሞ "ኦሆ ምስራቻ" በማለት ከፍ ባለ ድምጽ ይቀበላሉ፡፡ ከዋኙ እያንዳንዱን ስንኝ በዜማ ጀምሮ ሲጨርስ ተሳታፊው አሁንም "ኦሆ ምስራቻ" በማለት ከዋኙን ይቀበለዋል፡፡ ከዋኙ የመጨረሻውን ስንኝ ሲጨርስ ከተሰታፊዎቹ ጋር አብሮ "ኦሆ ምስራቻ" በማለት ይቀበላል፡፡ የመጨረሻውን "ኦሆ ምስራቻ" ዜማ ከዋኝና ተሳታፊ ዘጠኝ ጊዜ ከፍ ባለ ድምጽ ጀምረው ቀስ እያሉ ዜማውን ጠብቀው ይጨርሱታል፡፡ ተሳታፊው "ኦሆ ምስራቻ" የሚለውን ዜማ ተቀብሎ  ሲጨርስ በቀኝ እግሩ መሬቱን በሃይል ይረግጣል፤ ምቱ የከበሮን ያህል ይሰማል፤ ከእግር ምቱ ጋር አብሮ መለከት ይነፋል፤ ከበሮውም ይመታል፡፡

የምስራቻ ዘፈን ጎሳ መሪው አንድም የመስዋዕት አቅርቦታቸውን በሰላም ጨርሰው ስለመመለሳቸው፣ ወይፈኑ ጮሆ መስዋዕቱ ወደ ላይ ስለማረጉ እና የአማኙ በደልና ኃጢአት ይቅር ስለመባሉ የሮቺን ማመስገኛ ነው፡፡ አንድም ደግሞ የሮቺ በምትኩ

[42] አቶ ወርቃፈራሁ አመነሸዋ 24/10/14 ዓ.ም. የብሔረሰቡ ተወላጅ፤ በሚዛን ቴፒ የጂ.አይ.ኤስ መምህር

ፍቅርና ደስታ፣ ሰላምና ጤና ፤ ምርኮ እና በረከት ለአማኙ እንደለቀቀ የሚያረጋግጥ የደስታ ዘፈን ነው። ዘጠኝ ጊዜ "ኦሆ ምስራቻ" በማለት ቀስ እያሉ አዝማቹን ማጠናቀቃቸው። በፈጣሪ ዘንድ የመሰማታቸው ማረጋገጫ መሆኑን ሲያጠይቅ ነው። ጋሻና ጦር በተሳታፊዎች መያዙም የደህንነት ማረጋገጫ መሆኑን ሲያመላክት ነው።



ፎቶ 2፤ የምስራቻ የደስታ ጭፈራ (በጥናቱ አቅራቢ)

ዘፈኑና ጭፈራው ካለቀ በኋላ ታዳሚዎቹ ወደ ጎጆዋቸው በየጎሳቸው እየተመሩ እንዲገቡና አረፍ እንዲሉ በቃበቾ አማካኝነት ይነገራል።

### 4.2.4. የስዕለት አቅርቦት ክዋኔ

የስዕለትና የመባ አቅርቦት ሥርዓት ክዋኔ፤ የመስዋዕቱና የምስጋናው ሥርዓት ክዋኔ እንደተጠናቀቀ የስዕለትና የመባ አቅርቦት ሥርዓት ክዋኔ እንደሚቀጥል በቃበቾው አማካኝነት ይነገራል። ቃበቾው ተሳታዎቹ ይዘው የመጡትን መባ ጋሻው ላይ ስዕለቶቻቸውን ደግሞ መሬት ላይ እንዲያስቀምጡ ያዛል። ከመባ እና ከመስዋዕት ማቅረቢያው በስተጀርባ ደግሞ ቃበቾው በግራ እጁ መሬት ላይ የተሰካ ጦር ፣ በቀኝ እጁ ደግሞ እርጥብ የዶቅማ ቅጠል በመያዝ ይቆማል። የጉዶ ኬሶ ተሳታፊዎች በእጃቸው የያዙትን የገንዘብ መባ፣ ያመጡትን ንጹህ ነጭ እጣን እና ከርቤ ጋሻው ላይ እና ከጋሻው ውጪ ባለ ስፍራ ያስቀምጣሉ። ተሳታፊዎቹ ያመጡትን ስዕለትና መባ አስቀምጠው ሲጨርሱ ወደ ቃበቾው በመሄድ ጎንበስ ይሉና ትከሻቸውን በዶቅማ ቅጠል ሶስት ጊዜ መታ መታ ይደረጋሉ። ስዕለት የተሳሉና ስዕለቱ የደረሰላቸው ተሳታፊዎች የተደረገላቸውን እየተናገሩ እና እልል እያሉ ደስታቸውን ሲገልጹ፤ ተሳታፊዎችም በእልልታ እና በጭብጨባ፤ በጡሩንባ እና በከበሮ ድምጽ ማጀባቸውን በተደረገው ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል።

ስዕለት ከሰመረላቸው የበዓሉ ተሳታፊዎች መካከል በግምት ከ35 እስከ 40 ዓመት የሚሞላት ሴት የበዓሉ ተሳታፊ ትነሳና ወደ ተሳታፊዎቹ ፊቷን አዙራ ትቆማለች፤ የተደረገላትንም እንዲህ ስትል መናገር ትጀምራለች፤

> ከዚህ በፊት አስራ አንድ ዓመት ሙሉ እኔና ባለቤቴ ከተጋባን ጀምሮ ልጅ ፈልገን ብንሞክርም እምቢ ብሎን በጣም አዝነን ስናለቅስ ነበር፡፡ ከሁለት አመት በፊት ግን ለጉዶ ልጅ ከሰጠኸኝ አንድ ጠቦት በግ አመጣለሁ፤ ስራህንም በአደባባይ አወራለሁ ብዬ ተሳልኩ፡፡ የአያቶቼም አምላክ አላሳፈረኝም፤ ከስምንት ወር በፊት ይሄው የምታዩትን አይነት ወንድ ልጅ አገኘሁ፡፡

በማለት በተደጋገመ እልልታ ደስተዋን ትገልጻለች፡፡ የበዓሉ ተሳታፊዎችም አብረዋት በጭብጨባ እና በእልልታ ፤ በጡሩንባ እና በከበሮ ድምጽ ያጅቧታል፡፡

በዚህ የመባ እና የስዕለት ክፍለ ጊዜ ከጎሳ መሪው እና ከቃበቾው ፊት ለፊት የተቀመጠው ጋሻ ፣ ከጋሻው በስተቀኝ መሬት ላይ የተሰካው ጦር ፣ መባ እና ስዕለት አቅራቢዎቹ በዶቅማ ቅጠል ጀርባቸው ቸብ ቸብ መደረጋቸው፣ ከጋሻው በስተግራ በኩል በለው ባዶ መሬት ላይ የሚቀርቡ ስጦታዎች ሁሉም ትርጉም አላቸው፡፡

መባ እና ስዕለት የሚቀመጥበት ጋሻ ጎሳ መሪውም ሆነ አያት ቅድመ አያቶቻቸው በተለያዩ የጦር ሜዳ ውሎዎች የሮቺ እየረዳቸው ድል ያደረጉበት በመሆኑ የበዓሉ ተሳታፊዎች ጋሻው ላይ የመባ እና የስዕለት መስዋዕታቸውን ሲያቀርቡ ቀጣዩ የህይወት ዘመናቸው በአሸናፊነት እና በደህንነት መዝለቁን መተማመኛ ማግኛ መንገድ ስለሆነ ነው፡፡ ከጋሻው በስተቀኝ የተሰካው ጦር ደግሞ መባ አቅራቢዎቹ ቀጣዩ የህይወት ዘመናቸው የስኬት እና የብልጽግና ይሆናል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ከጋሻው በስተግራ ባለው መሬት ላይ ተሳታፊዎቹ ያመጡትን ስጦታ የሚያስቀምጡበት መሬት ትርጉም ደግሞ የበዓሉ ተሳታፊዎች በቀጣይ በልባቸው ስዕለት የተሳሉ ናቸው፡፡ በሸካቾ ብሔረሰብ ባህል መሰረት መሬት የተማጽኖ፤ የመሰማት፣ የመረጋጋት እና የመስከን ምሳሌ ነው፡፡ ሰው መሬት ይዞ ከጸለየ እና መሬት ነክቶ አንዳች የፍቅር ስጦታ ካስቀመጠ በየሮቺ እንደሚሰማ ይታናል፡፡ ምክንያቱም ስዕለት የሚሳለው ግለሰብ በራሱ አቅም ምንም ማድረግ እንደማይችል አውቆ "ተሸንፌያለሁ፤ በራሴ ምንም ማድረግ አልችልም፤ በቀጣይ ህይወቴን የተረጋጋ አድርግልኝ፤ ችግሬንም የሮቺ ሆይ ተረዳ፤ የችግሬን ምለሽ ከሰጠኸኝ ይህንን ይህንን… ስዕለት አስገባልሃለው" የሚል አንድምታ አለው፡፡ አጋፋሪው በዶቅማ ቅጠል ሶስት ጊዜ ቸብ ቸብ ማድረጋቸው አንድም የዶቅማ ቅጠል ከግንዱ ተቆርጦ ሳይደርቅ ረዥም ጊዜ ይቆያል፤ ስለዚህ ህይወትህ ደረቅ አይሁን የሚለውን ትርጉም ይሰጣል፡፡ ሶስት ጊዜ ቸብ ቸብ መደረጉ ደግሞ ባርኮትን ማረጋገጫ ነው፡፡ በሸካቾ ባህል ሶስት ቁጥር የባርኮት ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል[43]፡፡ የመባው፣ የስዕለቱ እና የፍቅር ስጦታው መርሃ ግብር ከተጠናቀቀ በኋላ ጎሳ መሪው

---

[43] ቡ.ው አቴስታታ ዳኬቶ፣ ዘውዴ ግችላ፣ ዳምበራኖ አለሙ፣ ኦጎ ንገራሻ፣ ታምሩ ኮቶ፣ ወልታታ ባሀሩ፣ አምባሳደር አበራ በጭሮ፣ ወ/ሮ አሰገደች ሽታኖ ፣ንፈራሻ እሸቱ፣ፍቃዱ አውዶ፣ ቆመ ቆጭቶ29/09/2014ዓ.ም - አጽንኦቱ የራሴ ነው፡፡

አቴስታታ ዳኬቶ ሁለት እጃቸውን ወደ ስጦታው ዘርግተው የህዝቡን ስጦታ የሮቺ እንዲቀበል ጸሎት ያደርጋሉ፤

> ጉዶ ላይ የምትገኝ የአያቶቻችን የሮቺ ሆይ ይህንን የህዝብ መባ ተቀበል፤ የሰጡህን የፍቅር ስጦታም አንተ አስታውስ፤ እኒህ የቸገራቸው ያንተ ልጆች ናቸውና አትተዋቸው፤ የምህረት እጆችህን አንሳላቸው፡፡ ፍላጎታቸውንና ጎዶሏቸውን አንተ ሙላ፡፡ የሮቺ ሆይ ስዕለታቸውን ስላሰመርክላቸው ልጆችህም አመሰግንሃለው፡፡ አሁንም አንተ ቤታቸውን ሙሉ አድርግ፡፡ ባርካቸው፡፡ በሽታን ከነሱ ላይ አርቅ፡፡ ዛሬ ከፊትህ ይዘው የተገኙትን ስጦታ በፊትህ እናቀርባለን፡፡ እጣንና ከርቤውንም በፊትህ እናጨሳለን፤ አንተ መልካም የሆነውን መዓዛ አሽትተህ ተቀበል፡፡ ህየወታቸውንም መልካም መዓዛ እንዳለው እጣንና ከርቤ አድርግላቸው፡፡

ብለው እንደጨረሱ ሁለት የጎሳ መሪው አገልጋዮች ከትልቅ ገል በተሰራ ማንደጃ ቀድሞ ለሚቃጠለው መስዋዕት ከተቀጣጠለው የእሳት ፍም ይዘው በመምጣት ከጎሳ መሪው ሁለት ሜትር ያህል ራቅ አድርገው ያስቀምጣሉ፡፡ ጎሳ መሪው ከፊት ለፊታቸው ያለውን የከርቤ እና የነጭ እጣን ስጦታዎች ከሁሉም ትንሽ ትንሽ በመውሰድ እሳቱ ላይ ይጨምራሉ፡፡ ተሳታፊው እንደተለመደው በእልልታና በጭብጨባ ይቀበላቸዋል፡፡ ጭሱ ቀጥ ብሎ ወደ ሰማይ ማረግ(መውጣት) ይጀምራል፡ ፡ ይህን የእጣን ጭስ እርገት የተመለከቱ ተሳታፊዎች አብዝተው ሲያጨመጭቡ፤ አካባቢውን በእልልታ ሲያቀልጡ፤ ጡሩንባው ሲነፋ፤ ከበሮውም ሲደለቅ በተደረገው ምልክታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህ ጊዜ ቃበቸው ይበልጥ እልል እንዲባል፤ እንዲጨመጨብ ጡሩንባውም ይበልጥ እንዲጮህ ከበሮውም ይበልጥ እንዲደለቅ በእጃቸው እንቅስቃሴ ይጠቁማሉ፡፡ ጭብጨባውና እልልታው ይቀጥላል፡፡

የሌላኛው የሸካቾ ጎሳ መሪ ምስራቾ የሚለውን ቀደም ሲል በሌላኛው ከዋኝ የተከወነውን የደስታ ዘፈን ያስጀምራሉ፡፡ ህዝቡም እየተቀበለ ምስራቾን አብሮ ያዜማል፡፡

የጎሳ መሪው አቴስታታ ዳኬቶ በደስታ ቆመው ጭስ ጭሱን እየተመለከቱ የትንቢት አይነት መልክ ያለውን ንግግር ማድረግ ይጀምራሉ፤

> የሮቺ ጸሎታችሁን ሰምቷል፤ ደስ ይበላችሁ፡፡ ቀጣዩ ዘመን ለሸካቾ ህዝብ ያማረ ይሆናል፡፡ ሰላምና ጤና ህዝቡ ያገኛል፡፡ እንስሳቱ ይረባሉ፡፡ ወተት እሸቱ ይበረክታል፡፡ ምርት ረድኤት ይወርድበታል፡፡ ሰላም ይሆናል፤ ይህ ሁሉ የሚታየው ችግር፤ ረሃብ ጦርነትና መገዳደል ቢቆይ ጥቂት ጊዜ ነው፤ ብዙ አይዘልቅም፤ ደስ ይበላችሁ፡፡ በህዝቡ ዘንድ ፍቅር ይጠነክራል፡፡ የሚጣላ የሚጋደል አይኖርም፡፡ ደስ ይበላችሁ የለቅሶና የዋይታ ዘመን ሊቋጭ ተቃርቧል፡፡

ብለው ጎሳ መሪው ሲጨርሱ ተሳታፊው ይበልጥ በደስታ ሲቃ ተሞልቶ በሚቆራረጥ እልልታና ጭብጨባ ይቀበላቸዋል፤ከተሳታፊው አይን ላይ የደስታ እንባ ሲያቆረዝዝ፣ ተሳታፊው የደስታ እንባ ሲያነባ መመልከት ተችሏል፡፡

ትንቢቱ ለመፈጸሙ ተሳታፊው በሙሉ ልብ እርግጠኛ ነበር፡፡ ምክንያቱም የጎሳ መሪው ትንቢት መሬት ጠብ አይልም ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ እስከዛሬ የተናገሩት በጠቅላላ ተፈጽሟል[44]

የከርቤ እና የነጭ እጣን ምሳሌ፤ አንድም መዓዛ ያጣ ህይወትን የማረና የተዋበ ህይወት እንዲኖር ያደርጋል፤ አንድም መንፈሳዊ ህይወት እንዳይሳከር ያደርጋል፤ አንድም ደግሞ ጉዶ ላይ የተመረቀው፣ የተጸለየው፣ የተለመነው ሁሉ እንዲሰምር ያደርጋል ተብሎ ስለሚታመን አማኙ አብዛኛውን ጊዜ ወደ ጉዶ ሲሄድ እጣንና ከርቤ ይዞ ይመጣል፡፡ የእጣኑ ጭስ ወደላይ ቀጥ ብሎ መውጣቱ አንድም የሮቺ የህዝቡን ጸሎት በሚገባ መስማቱን ማረጋገጫ ሲሆን አንድም ደግሞ የሚቀጥለው ዘመን ለሸካቾ መልካም ዘመን እንደሆነ ጥቆማ መስጠቱን ለማጠየቅ ነው[45]

### 4.2.5. ማዕድ የመቋደስ ክዋኔ

ማዕድ የመቋደስ ሥርዓተ ክዋኔ፤ ልክ ከቀኑ ስምንት ሰዓት ላይ እንደሚቀጥል ቃበቾው ለተሰበሰበው የበዓሉ ተሳታፊ ይናገራል፡፡ በዓሉ ቀጥሎ በነበረበት ወቅት ጉዶ አካባቢ ባለ ትንሽ አጸድ ውስጥ በተሰራ አዳራሽ በስዕለት[46] የመጣው ጠቦት ታርዶና ተጠባብሶ ይዘጋጃል፡፡ በገፐኢንዴዋ(የጎሳ መሪው የመጀመሪያ ባለቤት)

---

[44] የጎሳ መሪው ትንቢት በአብዛኛው ተፈጽሟል፡፡ የሩቁን ትተን ከዛሬ ሶስት አመት በፊት የተነበዩትን እንመልከት፡፡ በሸካቾ ውስጥ በሚኖሩ ብሔረሰቦች መካከል ከባድ እልቂት ይፈጸማል ግን ብዙም አይቆይም' ብለው ተነበዩ፤ ከ8 ወራት በኋላ ዘግናኝ ግጭቶች በሸካ ምድር ተከሰቱ፤ የብዙ ሰዎችን ህይወትም ቀጠፈ፡፡ ይሁንና ብዙም ሳይቆይ በእርቅ እና በሽምግልና ያማረ ሰላም ወረደ፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን የጎሳ መሪው ሰማይና ምድር ጭምር ይታዘዙላቸዋል፡፡ ዝናብ ከበዛ ተማጽነው ዝናብ እንዲቀንስ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ዝናብ ቢጠፋ ዝናብ ይሁን ማለት ብቻ በቂ ነው፤ ይዘንባል፡፡ ሸካቾ አንድም ጊዜ በድርቅና በረሃብ ስሙ ተጠርቶ አያውቅም፡፡ የቅርብ ጊዜ አስደናቂ ስራቸውን ላጫውትህ፡፡ ጠቅለይ ሚኒስትር ዓብይ አህመድ ክልል ውስጥ የተነሳውን ችግር አስመልክቶ ከህዝቡ ጋር ለመምከር ህዝብ ማሻ ከተማ ስታዲየም ተሰበሰበ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩም ከሄሊኮፕተር ወርደው ህዝቡን ሰላም እያሉ ወደተዘጋጀላቸው ስፍራ ሄደው ተቀመጡ፡፡ ንግግር ሲጀምሩ በረዶ የቀላቀለ አደገኛ ዝናብ መዝነብ ጀመረ፡ ፡ የጎሳ መሪው አቴስታታ ዳኬቶ መጥተው ቀኝ እጃቸውን ወደላይ በማድረግ ለ1 ደቂቃ ጸለዩ፡፡ አንድ ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ዝናቡ ቀጥ ብሎ ወዲያው ያማረ ጸሃይ ወጣ፡፡ ይህን ክስተት ዋልታ ቴሌቪዥን ዘግቦታል(ቃ.መ. ዳምቤራኖ አለሙ 28/9/14 ዓ.ም)፡፡

[45] ቡ.ው አቴስታታ ዳኬቶ፤ ኦጎ ንፈራሻ፣ ዳንበራኖ አለሙ 08/09/14 ዓ.ም) አጽንኦቱ የራሴ ነው፡፡

[46] በዕለቱ ለቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቱ ዝግጅት ሲባል፤ አንዲት ጠቦት በአንዲት ሴት በስዕለት መልክ የገባ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ "በተፈጥራዊ መቼቱ(አጽንኦቱ የራሴ ነው) ላይ 1966 ዓ.ም በፊት ባሉት ዓመታቶች ለበዓሉ ተሳታፊዎችና ታዳሚዎች ከ20 እስከ 30 ከብቶች ለእርድ ይቀርቡ ነበር፡፡ እነዚህ ከብቶች በኣብዛኛው በስዕለት የሚገቡ ሲሆን የተወሰኑት አቅም ካላቸው የበዓሉ ተሳታፊዎች በመዋጮ ተገዝተው የሚቀርቡ ናቸው፡፡ የሚጠጣውና ማባያው ደግሞ በገበኢንዴዋ አስተባባሪነት የሚሰራ ሲሆን የአካባቢው ሰዎችም ለጉዶ እያሉ በንጽህና ያዘጋጁትን ከቤታቸው እያመጡ ዳስ ውስጥ ያከማቹ ነበር፡፡ በጥንቱ የጉዶ ከበራ ወቅት በርካታ ስጦተዎች ይገቡ ስለነበር ደሃ ለሆኑ የጎሳው አበላት እና ለአካባቢው ነዋሪዎች ይከፋፈል ነበር፡፡ በእህልና በጥራጥሬ መልክ የሚገባ ስዕለትም ስለነበር ደሃው የዓመት ቀለቡን ከጉዶ ያገኝ ነበር፡፡ አሁንም ቢሆን መጠኑ ይነስ እንጂ በስዕለት ከሚገቡት መካከል ከግማሽ በላዩ ለድሆች ይከፋፈላል (ቃ.መ አምባሳደር አበራ በጭሮ 30/09/14 ዓ.ም)፡፡

የተዘጋጁ የብርዝ፣ የጠጅ፣ የጤፍ ጠላ እንዲሁም፣ የጤፍ እንጀራ፣ ቆጮ፣ በጮ እና አይቤ ይቀርባል፡፡ ቀደም ሲል እነዚህን ምግቦችና መጠጦች የሚያዘጋጁ አካላት የመንጻት ሥርዓትን የፈጸሙ እንደሆኑ ተጠቁሟል፡፡ በዚህ መልክ የተዘጋጀው ማዕድ፡፡ ለተሳታፊዎችና ለታዳሚዎች በሌማት በሌማት(ስንደዶ እና አክርማ ከሚባል የሳር አይነቶች የተዘጋጀ የማዕድ ማቅረቢያ) እየተደረገ ይቀርባል፡፡ በዚህ ሰዓት፤ የጎሳ መሪው ማዕዱን ሊባርኩ ይነሳሉ፤ "የሮቺ የቀረበውን ማዕድ ይባርክልን ይቀድስልን፡፡ እኛ እዚህ ስንቋደስ ሌሎች በየቤቱ ምንም የሌላቸው፤ የተጠሙ፣ የተራቡ የታረዙ አሉና የሮቺ ከማያልቀው በረከቱ ያጥግብልን፡፡" ብለው እንደጨረሱ ማዕዱን ከበው በየጎሳቸው የተቀመጡ የበዓሉ ተሳታፊዎች የቀረበውን መቋደስ ይጀምራሉ፡፡ በማዕድ ወቅት ያዝ እቺን… እቺን ብላ እሄን ውሰድ ከሚሉ ትንንሽ የግብዣ ድምጾች በስተቀር ምንም አይሰማም፡፡ በገበታ ወቅት ድምጽ አለመሰማቱ በሽካቾ ባህል አንድም ገበታ ክቡር በመሆኑ አንድም ደግሞ በተለይ በማንጻት ሂደት ውስጥ አልፎ የቀረበ ገበታ ፍጹም ንጹህ፣ ፍጹም ቅዱስ ስለሆነ ጤናንም የመፈወስ ሃይል አለው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ በገበታ ወቅት ሁሉም በአርምሞ የቀረበውን ማዕድ ይቋደሳል[47]፡፡

### 4.2.6. የምርቃት ክዋኔ

የምርቃት ሥርዓተ ክዋኔ፤ ማዕዱ ከፍ ካለ በኋላ፤ ልክ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን የአቴሶ ጎሳ መሪ አቴስታታ ዳኬቶ ተነስተው ይቆማሉ፡፡ ከሳቸው ጋር ሌሎች ጎሳ መሪዎች አብረው ይቆማሉ፡፡ በመጀመሪያ አቴስታታ ዳኬቶ መመረቅ ይጀምራሉ፤

> የሮቺ ሆይ ይህን በዓል በሰላም ስላስጨረስከን እናመሰግንሃለን፡፡ ያቀረብነውን መስዋእት ወደህ ስለተቀበልከን እናመሰግንሃለን፡፡ አንተ የአያቶቻችን አምላክ ዛሬም እናከብርሃለን፡፡ ይህን በዓል ለማክበር እዚህ የተሰበሰቡትን ሁሉ ባርካቸው፤ እዘንላቸው፤ ራራላቸው፡፡ ኑሯቸውን አቃናላቸው፤ ላልወለዱ ፍሬ ስጣቸው፡፡ ቤታቸው በበረከት ይሞላ፡፡ እርሾችም መብልን ይስጡ፤ ጓሯቸው ሙሉ ይሁን፣ ቤታቸው ሙሉ ይሁን፡፡ በቤታቸው መቅሰፍት አይግባ፤ ልጆቻቸው ይባረኩ፣ ለቁም ነገር ይብቁ፤ ሽካቾ ይባረክ፣ ሽካቾ ትለምልም፣ ደኑ፣ አየሩ መልካም ይሁን፣ አፈሩ ይባረክ፣ ኢትዮጵያ ትባረክ፤ ኢትዮጵያ ትለምልም፡፡ ሰላም ይሁን፤ ፍቅር ይሁን፣ ጥላቻና መገዳደል ይጥፋ፡፡

ብለው ለሌላኛው የጎሳ መሪ የምርቃት ዕድል ይሰጣሉ፡፡

> እዚህ የመጣችሁ ሁላችሁም፣ እንደሽካ ምድር ለምልሙ፤ እርጥብ ሁኑ፤ እንደ ሽካ ጸሃይ ፊታችሁ ይብራ፤ እዚህ በዓል ላይ የተገኛችሁ ሁላችሁ የየሮቺ በጎነት ይጎብኛችሁ፡፡ ሰላም ሁኑ፡፡ መጥፎ አያግኛችሁ፡፡ መንገዳችሁ ቀና ይሁን፡፡ ትረፉ ተትረፍረፉ፡፡ ቤታችሁ፣ ቀያችሁ ሰላም ይሁን፣ ሙሉ

---

[47] ቃ.መ ንፈራሻ እሸቱ 21/ 09/ 14 ዓ.ም አጽንኦቱ የኔ ነው፡፡

> ይሁን፡፡ አየሩ ሰላም ይሁን፣ ደናችን ይለምልም፡፡ ወንዞቻችን ሙሉ ይሁኑ፤ ምንጮቻችን አይድረቁ፤ ጨፌዎቻችን ይለምልሙ፡፡ ከዚህ በዓል ወደየቤቶቻችሁ የምትሄዱ ክፉ አያግኛችሁ፡፡ ሸካቾ አማቾቹን ይወዳል ከራሱ ይልቅ ባዕዳንን ያቀርባል፡፡ እናንተም ወዳችሁን እዚህ የተገኛችሁ ከእኛ በላይ ለምልሙ፡፡ እጃችሁ ይባረክ፣ ቤታችሁ ይባረክ፡፡ የነካችሁት ሁሉ ይባረክ፡፡

ብለው ምርቃቱን መጨረሳቸውን ለጎሳ መሪው ያሳውቃሉ፡፡ ጎሳ መሪውም የጉዶ ከበራ በዚሁ እንዳበቃ ተናግረው ተሳታፊውን ይሸኛሉ[48] በተደረገው ምልክታም ይኸንኑ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ሁለቱ የጎሳ መሪዎች ቆመው ተሳታፊውን ሲመርቁ፣ ተሳታፊው ከፍ ባለ ድምጽ ሁለት እጆቹን ወደ ፊት ዘርግቶ "አሜን አሜን አሜን..." በማለት ምርቃቱን ይቀበላል፡፡ ከፍ ባለ ድምጽ የመቀበሉ ምክንያት፤ ጉዶ ላይ ጎሳ መሪዎች መስዋዕት አቅርበው የመረቁት ምርቃት መሬት ጠብ እንደማይል፣ የመረቁት እንደሚመረቅ፣ የረገሙት የተረገመ እንደሚሆን፣ ለዚህም ከየሮቺ ስልጣን እንደተሰጣቸው፣ በሸካቾ ብሔረሰብ ስለሚታመን ነው፡፡

የሸካቾ ብሔረሰብ በጎሳ መሪዎች አማካኝነት የተመረቁ ሰዎች ሲለመልሙ፤ የተረገሙ ደግሞ መቅሰፍት ወደቤታቸው ሲገባ ሁሉንም በታሪክ ሂደት ውስጥ አስተውሏል[49] በማለት የዚህ ጥናት መረጃ አቀባዮች ይናገራሉ፡፡

### 4.3. የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ሥርዓተ ክዋኔ በበዓል ማግስት

የጉዶ ኬሶ በዓል በዕለተ ቀኑ ከተጠናቀቀ በኋላ የጎሳ መሪዎች እና ተሳታፊዎቹ በጉዶ አካባቢ የታረደው እርድ፣ የቀረበው መጠጥ ተበልቶና ተጠትቶ እስኪጠናቀቅ ድረስ ለአራት ቀናት ያህል ይቆያሉ፡፡ በእነዚህ ጊዜያት የበዓሉ ተሳታፊዎች በየዳሳቸው ሆነው ገበታቸውን ከተቋደሱ በኋላ ሰብሰብ እያሉ ይጫወታሉ፡፡ በጭውውታቸው የተቀያየሙ በጎሳ እና በባህል መሪዎች አማካኝነት ይታረቃሉ፡፡ ስለ አካባቢው ደህንነት፣ ስለ ደኑ፣ ስለ ወንዙ፣ ስለጨፌው ያወራሉ፡፡ በቀጣይ ምን ይደረግ? ባለፈው ደን ውስጥ ማን ገብቶ አደነ? ማንስ ዛፍ ቆረጠ? ምን ምን ውሳኔዎች ተሰጡ? በአከባቢው የተጣሉ እና የተቀያየሙ አሉን? ብለው እየተጠያየቁ ለማስታረቅ ቀጠሮዎችን ይይዛሉ፡፡ በአራተኛው ቀን በጊዜያዊነት የተሰሩ ጎጆዎች በተሳታፊዎቹ ይፈርሳሉ፡፡ የፈረሰው እንጨት ለሌላ ጊዜ እንዲሆን በጎሳ መሪው ግቢ ውስጥ ይቀመጣል፡፡ በአራተኛው ቀን ስምንት ሰዓት ላይ የጎሳ መሪው አገልጋዮች እና ከፊል ተሳታፊዎቹ ጎሳ መሪውን አጅበው ቤታቸው ያደርሳሉ፡፡

---

48 በተፈጥራዊ መቼቱ የጉዶ ኬሶ ክዋኔ በ አንድ ቀን አያልቅም፡፡ እርግጥ ሙሉ የመስዋእቱ፤ የአምልኮና የምስጋና ስርዓቱ በመጀመሪያው ቀን ላይ የሚጠናቀቅ ቢሆንም፡፡ ለጉዶ የተዘጋጀው ምግብ እስኪያልቅ ቢያንስ እስከ አራት ቀናት ድረስ ተሳታፊው የመንጻትን ህግ ሳያጓድል ራሱን እየጠበቀ በተዘጋጀው ጎጆ ውስጥ እያደረና እየዋለ እዛው ይቆያል፡፡ ቤቱ አይሄድም፤ ከሄደም ዳግም አይመለስም ምክንያቱም ሄዶ ከተመለሰ እርኩስ የሆኑ ነገሮች ያገኙታል፤ ተሳታፊውንም፤ ስፍራውንም ያረክሳል ተብሎ ስለሚታመን ነው (ቃ.መ አምባሳደር አበራ 02/10/14 ዓ.ም)፡፡

49 ቃ.መ ወልታታ ባህሩ 28/08/14 ዓ.ም

የጎሳ መሪው ቤት በሴሲኖ ዛፍ የታጠሩ እና  ከፊት ለፊቱ ሶስት ቅጥሮች ያሉት ሲሆን የመንጻት ስርዓትን ያልፈጸመ ሰው አንደኛውን አጥር አልፎ ወደ ሁለተኛው አይገባም፡፡ ይህ ሁል ግዜም በጎሳ መሪው ቤት ተግበራዊ የሚሆን ነው፡፡ ንጹህ የሆነ ሰው ካለ ግን የመጀመሪያውን አጥር አልፎ ሁለተኛው አጥር ጋር ይቆማል እንጂ ወደ ሶስተኛው አጥር ዘልቆ አይገባም፡፡ አቻ ጎሳ መሪ ከሆነ ብቻ ነው ወደ ሶስተኛው አጥር የሚጠጋው፡፡ ኋላም የጎሳ መሪው ሲፈቅዱ ወደ ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን ሌሎች ሰዎች ባሉበት ሆነው፤ ጎሳ መሪው ናቸው በረንዳ ላይ ሆነው የሚያናግሯቸው፡፡

ጎሳ መሪውን አጅበው የሄዱ ተሳታዎች ዝም ብለው አይመለሱም፡፡ በጎሳ መሪው ቤት ፍየል ይታረድላቸዋል፡፡ የታረደላቸውን እየበሉና ከጎሳ መሪው ጋር እየተጨዋወቱ አድረው በአምስተኛው ቀን ሶስት ሰዓት ላይ ተመራርቀው ይለያየሉ፡፡ ጎሳ መሪው

> ለቀጣዩ ጉዶ ሁላችንንም በህይወት የሮቺ ያድርሰን፡፡ ቀጣዩን አመት የሮቺ ምርቱን ያትረፍርፍልን፡፡ ሁሉ ሰራተኛ ይሁን፡፡ የሚቦዝን አይኑር፡፡ የነካችሁት ይለምልም፤ የምትወልዱት ይባረክ፡፡ ስታወሩ ተደመጡ፡፡ ያያችሁ ይውደዳችሁ፡፡

ብለው ጎሳ መሪው ከመረቁ በኋላ ሌላኛው ጎሳ መሪ ኦጎ ንገራሻ የሚከተለውን ምርቃት አቴስታታ ዳኬቶን ይመርቃሉ፡፡

> በዘመንዎ ክፉ አይዩ፡፡ የየሮቺ መንፈስ ከእርስዎ ጋር ይሁን፡፡ ጎሳዎ ይታዘዝዎ፡፡ አሁንም የመፍትሄ ሰው ሁኑ፡፡ አሁንም የመረቁት የተመረቀ ይሁን፡፡ የረገሙት ይረገም፡፡ እድሜዎ ይርዘም፡፡ በቤትዎ የገባ የተመረቀ ይሁን፡፡ በሰላም ያገናኘን፡፡

ብለው ይመርቋቸዋል፡፡ አቴስታታ ዳኬቶም ጎንበስ ብለው "አሜን አሜን አሜን" ይላሉ፡፡ ከምርቃቱ በኋላ አቴስታታ ዳኬቶ "ከሚቀጥለው አመት ጀምሮ ህዝቡ ወደ ስራ እንዲሰማራ ይሁን፡፡ ስራ ፈት አይኑር፡፡ እዚህ የገባውን ስዕለትም ሆነ ስጦታ ተሸጦም ይሁን በተገኘው አጋጣሚ ለድሆች ይከፋፈል" ብለው ለቃበኞው መመሪያ ሰጥተው፤  ቤታቸው ያሉትን እንግዶቹ ሲሸኟቸው በምልከታው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 5. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የጉዶ ኬሶ ሀገረሰበዊ እምነት ሥርዓተ ክዋኔን ተንትኗል፡፡ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት፤ የጉዶ ኬሶ ሀገረሰባዊ እምነት ሥርዓተ ክዋኔ ሂደት ምን ይመስለል? በጉዶ ክዋኔ ወቅት የሚቀርቡ ቴክስቶች፣ ቁሶችና ድርጊቶች ምን አይነት ትዕምርት አላቸው? የጉዶ ኬሶ ክዋኔ በመከወኑ የሚገኘው ጥቅምና ባይከወን ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ምንድን ነው? የሚሉ መሪ የምርምር ጥያቄዎች ተነስተው በጽሁፉ መልስ አግኝተዋል፡፡

በሸካቾ ሀገረሰባዊ የእምነት መዋቅር ውስጥ ግዛቱን በሰማያት ያደረገው ፈጣሪ(የሮቺ) ከምድራዊው ሰዎች ጋር በአምልኮ አማካኝነት ግንኙነት የሚፈጥርበት ጉዶ ኬሶ የሚባል ቅዱስ ስፍራ አለ፡፡ ይህ ቅዱስ ስፍራ ከፍ ያለ ተራራና በደኖች የተከበበ ሲሆን የሸካቾ ብሔረሰብ በሰባት ዓመት አንድ ጊዜ በዚሁ ቅዱስ ተራራ ላይ በመገኘት የበኩር የሆነውን ምርት ለየሮቺ መስዋዕት በማቅረብ የሚያከብረው የመባ እና የምስጋና ክዋኔ መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

እንደ ሸካቾ ብሔረሰብ ጎሳ መሪዎች ገለጻ በሸካቾ ብሔረሰብ የጉዶ ኬሶ ሥርዓተ ክዋኔ የተጀመረው ብሔረሰቡ በንጉስ ሰለሞን ዘመነ መንግስት ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ ሲፈልስ እስራኤላውያን በአብርሃም አማካኝነት ለአምላካቸው በተራራ ላይ የሚያቀርቡትን የመስዋዕት ሥርዓተ ክዋኔ ይዘው እንደመጡና ይህንኑ ክዋኔ ማስቀጠል እንደቻሉ በጥናቱ ተጠቁሟል፡፡

የጉዶ ኬሶ የመስዋዕት ሥርዓተ ክዋኔ የሚከወነው ፤ ፈጣሪ(የሮቺ) ለብሔረሰቡ ስላደረው መልካም ነገር፣ ስላበዛላቸው በረከት፣ ስላሰፈነላቸው ሰላም፣ ስለሰጣቸው ጤና፣ ስላስጠበቀላቸው መልካም ስነምህዳር ሲሉ እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል፡፡

የጉዶ ኬሶ የመስዋዕት ሥርዓተ ክዋኔ ህግን በመተላለፍ የተከወነ እንደሆነ፣ ወደ ተቀደሰው ደን በመግባት ዛፎችንና እጽዋትን የተቆረጡ እንደሆነ፣ ከብቶችን የሚያሰማሩና ስፍራውን የሚዳፈሩ እንደሆነ፤ በተዳፈሩት ሰዎች ላይ መቅሰፍት ወደ ቤታቸው እንደሚገባ፣ አካባቢው እንደሚታወክ፣ የህዝቡ ጤና እንደሚጠፋ፣ ሰማይ መሬቱ እንደሚጣሉ፣ ምርት ረድኤቱን እንደሚያጣ በጥናቱ ተመላክቷል፡፡

በክዋኔው ማብቂያ ላይ ጎሳ መሪው ቀጣዩ ዘመን ለሸካቾ ብሔረሰብ ያማረ እንደሆነ፣ የህዝቡ ሰላምና ጤንነት እንደሚጠበቅ ፣ እንስሳቱ እንደሚረቡ፣ ወተት እሸቱ እንደሚበረክት ፣ ምርት ረድኤት እንደሚወርድበት መተንበያቸውን ፤ የክዋኔው ተሳታፊዎችም ትንቢታዊ አዋጁን በደስታ እንደተቀበሉ ጥናቱ አሳይቷል፡፡

**ማጣቀሻዎች**

ምህረት ካሳ፡፡ 2002 ዓ.ም፡፡ የሽካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የምግብ ዝግጅት እና አመጋገብ ስርዓት፡፡ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ስለሺ አባተ፡፡ 2002 ዓ.ም፡፡ የሽካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት፡፡ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

አበራ በጭሮ፡፡ 2014 ዓ.ም፡፡ *የሸካቾ ብሄረሰብ ታሪክና የባህል እሴቶች*፡፡ አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ፡፡

አማረ ሞላ፡፡1999 ዓ.ም፡፡ የሸካቾ ብሄረሰብ ሃገረሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና፡፡ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

አውግቸው ወርቅአገኘሁ፡፡1989 ዓ.ም፡፡ ትውፊትና ባህላዊ ክንዋኔዎች በሸካ ብሔር፡፡ በትያትር ትምህርት ክፍል፣ ለ ቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡

ወንድምስሻ አንገሎ፡፡2013 ዓ.ም፡፡ *እናርያን ፍለጋ*፡ አዲስ አበባ፣ ብራና በፃህፍት መደብር፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም፡፡ 1993 ዓ.ም፡፡ *አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ መፅሀፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ 1962 ዓ.ም፡፡ *መፅሀፍ ቅዱስ፡፡* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

*የመፅሃፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡* 1992 ዓ.ም፡፡ አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት፡፡

የሸካ ዞን ፕላን ኢኮኖሚ መምሪያ፡፡ 2014 ዓ.ም፡፡ ዓመታዊ ዕቅድ፣ ማሻ፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም፡፡ 1993 ዓ.ም፡፡ *አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

የደቡብ ክልል ብሔሮች፣ *ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፕሮፋይል፡፡* 2001 ዓ.ም፡፡ በብሔረሰቦች ምክር ቤት የብሔረሰቦች የጋራ እሴቶችን ማጎልበትና አለመግባባቶችን መፍታት ዋና የሥራ ሂደት ፣ ሃዋሳ፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ 2009 ዓ.ም፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርህዎችና አተገባበር*፡፡ አዲስ አበባ፣ ተፈራ ስዩም ፕሪንቲንግ ፕሬስ፡፡

ደስታ ተክለወልድ፡፡1962 ዓ.ም፡፡ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ 1991 ዓ.ም፡፡ *የስነቃል መምሪያ፡፡* አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ፍጹም ብርሃኑ፡፡ 2006 ዓ.ም፡፡ የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

Atkinson, P. 2004. Review Essay. *British Journal of Sociology of Education*, 25:1, 107-114.

Bauman, R. 1975. "Verbal Art as Performance." *American Anthropologist, New Series* (77).2, 290-311

Central Statistical Agency. 2010. “The 2007 Population and Housing Census of Ethiopia Result for SNNP Region.” Statistical Result on Population size and characteristics (part 1). Addis Ababa.

Cooke, B. and Macy, G. 2005. *Christian Symbol and Ritual. An Introduction*. New York: Oxford University Press.

Getaneh Haile, 2022. "The contribution of Gudo forest conservation culture is key to biodiversity conservation the case of Sheka Zone, southwest Ethiopia," Land Use Policy, Elsevier, vol. 113(C).

Jupp, Victor. 2006. *The Sage dictionary of social research methods*. Sage.

Kapchan, D. 1995."Performance" *Journal American folklore*, Vol.108, No, 433 Amarican Folklore society, 479-508.

Kothari, C. 1985. *Research Methodology, Methods and Techniques*. Indiya: new age international Limited Publisher.

O’Connor, B. 1995. Healing traditions: Alternative medicine and the health professions. Philadelphia: University of Pennsylvania Press.

Sims, M. C, and Stephens, M.2005. *Living Folklore:* An Introduction to the Study. Utah State University Press.

Werner J. Lange. 1982. History of the Southern Gonga (south western Ethiopia) the University of Michigan.

Wehmeier, Sally and others .2006. *Oxford Advanced Learner’s Dictionary of Current English.* 7th Ed, Oxford University Press,